# Addis Ababa City Administration Disaster Prevention, Control, Inspection and Qualification System Directive No. 163/2017

Addis Ababa City Administration Disaster Prevention, Control, Inspection and Qualification System Directive No. 163/2017

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና
አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን
Addis Ababa City Administration Fire and
Disaster Risk Management Commission

ኅዳር 1፥ 2017

## መመሪያ ቁጥር 163/2017

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ መከላከል፣ ቁጥጥር፣ ፍተሻና ብቃት ማረጋገጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 163/2017

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪዎች ህይወትና ንብረት እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ደህንነት ከማንኛውም አደጋዎች እንዲጠበቅ ማድረግና አስተማማኝ የሥራና የመኖሪያ አካባቢ ለመፍጠር፤

ከተቋማት ጋር ያለውን የስራ ትስስርና ግንኙነት ሥርዓት ባለው መልኩ አጠናክሮ ለማስኬድና የአፈፃፀም ሁኔታዎችን ለመከታተል የሚያስችል አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር የህላፊነትና የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የሚገኙ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ደህንነት ዝርዝር አፈጻጸምና የአሰራር ሂደቶችን ለመከታተል የሚያስችል ግልፅ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሠራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀፅ 16 (2) (ሠ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ደህንነት ደንብ ቁጥር 132/2014 አንቀፅ 25 መሠረት ኮሚሽኑ ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ መከላከል፣ቁጥጥር፣ ፍተሻና ብቃት ማረጋገጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር**163/2017 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "**ከተማ**"፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማለት ነዉ፤

2) "**መከላከል**"፡- ማለት ማንኛውንም በህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ድንገተኛ አደጋዎችን እንዳይከሰቱ የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ ነው፤

3) "**የጤና ተቋም**"፡- ማለት የሕክምና ወይም ሌላ ክብካቤ የሚሰጡ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ የማዋለጃ፣ የህጻናት ማሳደጊያ፣የአረጋውያን መንከባከቢያ ተቋማትን ያካትታል፤

4) "**ማረሚያ ቤት**"፡- ማለት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ታራሚዎች የተወሰነባቸውን የእስራት ቅጣት እንዲፈፀም የሚቆዩበት ተቋም ነው፤

5) "**መኖሪያ ቤት**"፡- ማለት ለመኖሪያነት የሚያገለግል አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎች ያሉት ህንጻ ነው፤

6) "**የንግድ ማዕከል**"፡- ማለት የተለያዩ ቁሳቁስ ማከማቻ፣ መገበያያ እና ሸቀጣ-ሸቀጦችን ለማሳየት ወይም ለመሸጥ የሚውል ሕንፃ ነው፤

7) "**የገበያ ማዕከል**"፡- ማለት የገበያ አዳራሽ፣ ሱፐር ማርኬት፣ሬስቶራንት፣የመድሃኒት ቤት፣ያገለገለ እቃ መሸጫ፣ የደረቅ እና የተዘጋጁ ምግብ ነክ ነገሮችን፣ ከብረት የተሰሩ እቃዎች ወይም የግንባታ መሳሪያዎች አቅርቦቶችን፣ የማሳያ ክፍሎችን፣ የማጫረቻ ክፍሎችን፣ ለጥቃቅን የንግድ ስራዎች የሚያገለግሉ ህንጻዎችን ከሸቀጣሸቀጥ ሽያጭ ጋር የተያያዙ የጽ/ቤት፣ የማከማቻና የአገልግሎት መስጫዎች እና በመተሳሳይ ሕንፃ ውስጥ የሚገኙ ስፍራዎች የንግድ ህንጻዎች ያጠቃልላል፤

8) "**ኢንዱስትሪ**"፡- ማለት የተለያዩ አይነትና ባሕሪያት ያላቸውን ምርቶች የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን ሆኖ ምርት ማቀነባበር፣ መገጣጠም፣ መፈታታት፣ መደባለቅ፣ ማሸግ፣ ማጠናቀቅ፣

ማሳመር፣ መጠገንና እቃውን ወደነበረበት መመለስ ወይም መሰል ተግባራትን የሚያከናዉኑ ተቋማትን ያካትታል፤

9) "**ቅይጥ አገልግሎት የሚሰጥ ህንፃ**"፡- ማለት በአንድ ህንጻ ላይ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የተለያየ አገልግሎት የሥራ ዘርፍን ማከናወን ነው፤

10) "**የህንጻ አደጋ**"፡- ማለት የሕንፃውን ተጠቃሚዎች ሕይወት እና ንብረት አደጋ ላይ የሚጥሉ የእሳት መነሳትና ስርጭት፣ የጭሶች ወይም ጋዞች መፈጠር፣ የፍንዳታ ወይም የሌሎች በሰዉ ሰራሽ እና በተፈጥሮ ምክንያት በህንጻዎች ላይ የሚከሰት አደጋ ነው፤

11) "**ምድብ አንድ ህንጻ**"፡- ማለት ባለ አንድና ባለሁለት ወለል አነስተኛ ህንጻ ነው፤

12) "**ምድብ ሁለት ህንጻ**"፡- ማለት ከአንድ እስከ ስድስት በተደራራቢነት ያለው መካከለኛ ህንጻ ነው፤

13) "**ምድብ ሦስት ህንጻ**"፡- ማለት ከስድስት ወለል በላይ በተደራራቢነት ያለው ከፍተኛ ህንጻ ነው፤

14) "**የትምህርት ተቋም**"፡- ማለት ለትምህርት ዓላማ የሚውል ሕንፃ ሆኖ ዩኒቨርስቲዎችን፣ ኮሌጆችን፣ መሰናዶ ተምህርት ቤትን እና መሰል ተቋማትን ያካትታል፤

15) በደንብ ቁጥር 132/2014 ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጋት ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኝ ተቋም እና በተገነቡ፣ በመገንባት ላይ ያሉ እንዲሁም ወደፊት በሚገነቡ ህንጻዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የደህንነት መስፈርት

## 4. የማተሚያ ድርጅት የደህንነት መስፈርት

1) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

2) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

3) በህንጻው ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ፣ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

4) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

5) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

6) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

7) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

8) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

9) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

10) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

11) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

12)አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

13)በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

14)በህንጻው ውስጥ ወይም ውጭ የተገልጋዩን ቁጥር ያገናዘበ በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ሊኖረው ይገባል፣

15)በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

16)በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

17)እንደ የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ባህሪና የተቀጣጣይነት ደረጃ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ እስከ 150 ሺ ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

18)ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጋራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

19)የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

20)በህንፃዎችና በተለያዩ ተቋማት ስራ ባህሪ ተጋላጭነትና አጋላጭነትን መሰረት ያደረገ የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

21)ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

22)ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

23) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

24) በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

25) በማተሚያ ድርጅት ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

26) በማተሚያ ድርጅት የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

27) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

28) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

29) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

30) በ ህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

31) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

32) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

33) በህትመት ክፍል ውስጥ ከአንድ ሜትር ያላነሰ ስፋት ያለው መተላለፊያ መንገድ ሊኖር ይገባል፤

34) ለእሳት አደጋ መፈጠር ምክንያት የሚሆኑ ተቀጣጣይ የህትመት ቁሶችን እንደየመቀጣጠል ባህሪና ደረጃቸው በመለየትና ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ማከማቸት አለበት።

## 5. ነዳጅ ማከማቻ ዲፖ የደህንነት መስፈርት

1) ሁለት መቶ ሺ ሊትር እና ከዛ በላይ ሊይዝ የሚችል ከመሬት በላይ የሚዘጋጅ የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ በማራገፍ ሂደት የሚኖር ነዳጅ ፍሰትን ለመከላከል የሚያስችል አዉቶማቲክ የሆነ መቆጣጠሪያ ሊገጠምለት ይገባል፤

2) የነዳጅ ማከማቻ ዲፖ የጋኑ ዉጫዊ አካል በፋይበር ግላስ ወይም ተመሳሳይ የዝገት መከላከያ ቅብ ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት፤

3) የነዳጅ ማከማቻ ዲፖ ጋኖች ከ አንድ ሜትር ባላነሰ ጥልቀት፣ ስድስት ሚሊ ሜትር ያላነሰ ዉፍረት ካለዉ ላሜራ ፣ የላሜራው ቅጥያና ወይም ብይድ በ0.4 ባር የአየር ግፊት የተፈተሸና ከጋኑ የሚገናኙ ቱቦዎች ከማንኛውም ፍሰት ነፃና የማይዝግ ሆነው ከመሬት በታች እንዲቀበሩ ተገርገው መዘጋጀት አለባቸው፤

4) የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ ስፍራ የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር ዉሃ ከሚወጣበት ቦታ ሃምሳ ሜትር ርቀት ሊኖረው ይገባል፤

5) ከታንከሩ በላይ የሚዘጋጀዉ የኮንክሪት ሽፋን የዉፍረት መጠን ከ20 ሴ.ሜትር በላይ ውፍት እንዲኖረው ተደርጎ ጋኖቹ ከመሬት ጋር በብሎን ታሳሪ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፤

6) ዴፖዉ ቢያንስ ለሁለት ሰዓት ያህል እሳትን ለመከላከል የሚያስችል ከአንድ መቶ ሃምሳ እስከ ሁለት መቶ ሜትሪክ ኪዩቢክ የመያዝ አቅም ያለዉ በቂ የፎም ዉሀድ፣ ከሃምሳ እስከ ስልሳ ሜትር ርቀት ሊወረዉር የሚችል ፎም ሞኒተር፣ አንድ ባለ ሃምሳ ኪሎ ግራም ድራይ ፓውደር እንዲሁም እሳትን በዉሃ ለማቀዝቀዝ የሚያስችል ስፕሪንክለር ሲስተም ሊዘጋጅ ይገባል፤

7) ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ የነዳጅ መያዣ ጋኖች ባሉበት ስፍራ የአካባቢ ስነምህዳር ተስማሚነት ለመጠበቅ በማራገፊያና መጫኛ ዙሪያ በኮንክሪት የተገነባ የፍሳሽ መቆጣጠሪያና መሰብሰቢያ ማዘጋጀት እንዲሁም በዓመት ሁለት ጊዜ በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲወገድ ማድረግ ይገባል፤

8) የነዳጅ ማከማቻ ጋኖቹ በሦስት ሜትር ከፍታ በብሎኬት ወይም በድንጋይ ከተከለለው ዋና አጥር በሰላሳ ሜትር መራቅና በመግቢያ በር አካባቢ የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስርዓት የሚያሳይ ንድፍ ማዘጋጀት ይገባል፤

9) የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ ኩባንያ በየዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ የሚያበቃውን መስፈርት በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መውሰድና በየአመቱ ማሳደስ ይኖርበታል፤

10) የማጠራቀሚያን ጋን የነዳጅ መጠን በየቀኑ በመለካት የነዳጅ ጉድለት የሚታይበት ከሆነ በአስቸኳይ የማስተካከያ ዕርምጃ መውሰድ ይገባል፤

11) የተቀጣጣይ ባህሪውን መሰረት ያደረጋ በቂ ፎም ክምችት ከፋየር ፓምፕ ጋር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

12) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

13) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

14) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

15) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፤

16) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

17) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፣ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

18) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

19) በህንፃዎችና በተለያዩ ተቋማት ስራ ባህሪ ተጋላጭነትና አጋላጭነትን መሰረት ያደረገ የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

20) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

21) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

22) ነዳጅ ማከማቻ ዲፖ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

23) ነዳጅ ማከማቻ ዲፖ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

24) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

25) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

26) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

27) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

28) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት፤

29) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 6. የነዳጅ ማደያ የደህንነት መስፈርት

1) በነዳጅ ማደያ ደሴት፣ የነዳጅ ማራገፊያና የተሽከርካሪ እጥበት አካባቢዎች ለያንዳንዳቸዉ አንድ ባለ ዘጠኝ ሊትር ፎም የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ መሟላት ይገባል፤

2) ማደያዎቹ ከህንጻ ጋር ተያይዘዉ የሚገነቡ ከሆነ ከነዳጅ ማከማቻ ጋንና በህንጻዉ መሰረት መካከል ከ1.5 ሜትር ርቀት ያላነሰ ሊኖር ይገባል፤

3) የነዳጅ ትነት ማስወገጃዉ መስመር ከመሬት በላይ አምስት ሜትር ከፍታ፣ ከህንጻዉ አስር ሜትር ያላነሰ ርቀት፣ ከመስኮቶች፣ በሮች፣ ከህንጻዉ ግድግዳና የነዳጅ መቅጃዉ ፓምፕ ከ8 ሜትር ያላነሰ ርቀት እንዲኖረዉ ተደርጎ መጋጀት ይኖርበታል፤

4) በመኖሪያ መንደሮች መካከል የተገነባ የነዳጅ ማደያ የማደያዉ አጥር ከመኖሪያ መንደሮቹ የአምስት ሜትር ርቀት ሊጠበቅ ይገባል፤

5) በነዳጅ ማደያዉ ዙሪያ ያሉ ነዋሪዎች አስፈላጊዉን የእሳትና ሌሎች ድንተኛ አደጋ ጥናቃቄ እንዲያደርጉ ማስተማርና በየጊዜው ከእሳት ጋር የተገናኙ ሥራዎችን አደጋን እንዳይፈጥሩ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፤

6) የነዳጅ ውጤቶች የሆኑት የተለያዩ ዘይቶች ፣ ማለስለሻ ቅባቶች የማከፋፈል ሥራ የሚያከናውኑ ህንጻዎች ግንባታ እሳትን ለ30 ደቂቃ ያህል የመቋቋም አቅም ሊኖረው ይገባል፤

7. የነዳጅ ዉጤቶች የማከፋፈል ስራ በሚከናወንበት ክፍል ከእሳት ጋር የሚኖረው ግንኙነት ከአንድ ሜትር በላይ መራቅ አለበት፤

8) ነዳጅ በተለያዩ ጥቃቅን እቃዎች በመቀናነስ ከቦታ ቦታ ይዞ መንቀሳቀስ፣ የተሸከርካሪ ሞተር እየሰራ፣ የህዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪ ተሳፋሪ ጭኖ ነዳጅ መቅዳት፣ የፕላስቲክ ምርት ውጤቶች የሆኑ እቃዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው፤

9) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

10) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

11) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

12) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

13) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

14) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፤ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

15) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሸከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

16) በህንፃዎችና በተለያዩ ተቋማት ስራ ባህሪ ተጋላጭነትና አጋላጭነትን መሰረት ያደረገ የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

17) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

18) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዩር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

19) በማደያ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

20) በማደያ ውስጥ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

21) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

22) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

23) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

24) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

25) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

26) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 7. የነዳጅ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የደህንነት መስፈርት

1) የተፈቀደለት ነዳጅ የሚጭን ተሽከርካሪ በመኪናዉ ሞተር፣ በሪሞርኬዉና በሼልቶዉ ላይ ለሚያጋጥም የእሳት ቃጠሎ አደጋ ማጥፊያነት የሚያገለግል በእጅ የሚያዝ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ በተገቢ ክብደትና አይነት ማሟላት ይገባዋል፤

2) የተፈቀደለት ነዳጅ የሚጭን ተሽከርካሪ ነዳጅ እንደጫነ የማደያ ጣቢያ ወይም ዴፖ ባለበት ስፍራ ውጭ መቆም ፣ነዳጅ የማንጠፍጠፍ ፤ ተሽከርካሪን በመደበኛነት እንዲያሽከረክሩ ፍቃድ ከተሰጣቸዉ አሽከርካሪዎች ዉጪ እንዲያሽከረክሩ መፍቀድ ፤ ከተፈቀደዉ ዉጪ ሰውም ሆነ ሌላ ቁስ መጫን ፤ ቅስፈታዊ ኤሌክትሪክ መፈጠር ምክንያት የሚሆኑ እንደ ቦብሊን፣ ሻማ የመሳሰሉ አልባሳትን መጠቀም ፈጽሞ የተከለከለ ነዉ፤

3) የተፈቀደለት ነዳጅ ጫኝ ተሽከርካሪ ከተፈቀደለት ስፍራ ውጭ ከመንገድ፣ ከአውራ ጎዳና፣ ከመተለላፊያ ወጣ ብሎ፣ ከፋብሪካ እና ከማንኛውም ተቀጣጣይ ነገሮች 8 ሜትር እንዲሁም ከማንኛውም ህንጻ 15 ሜትር ባላነሰ ርቀት ጠብቆ መቆም አለበት፤

4) የሁሉም የነዳጅ ካምፓኒ ነደጅ ጫኝ ተሽከርካሪ ሳልቬጅ ፓምፕ ማዘጋጀት አለበት፡

5) የተፈቀደለት ነዳጅ ጫኝ ተሽከርካሪው ላይ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የደህንት ምልክት ወርዱም ሆነ ቁመቱ ከሁለት መቶ ሰባአምስት ሚሊሜትር ያላነሰ እና የጽሁፉ ምልክት አርባ አንድ ሚሊሜትር በመሆን በጉልህ እንዲታይ ተደርጎ መዘጋጀትና መለጠፍ አለበት፤

6) ነዳጅ የጫኑ ተሸከርካሪ በእንቅስቃሴና በሙቀት ምክንያት የትነት መጠን በመጨመር በእንቅስቃሴ ላይ መንጠባጠብ እንዳያስከትል ህጉ በሚያዘው መሰረት መከናወን ይኖርባቸዋል፤

7) ነዳጅ በሚራገፍበት ቦታ ቦንዲግ ግራውንድ ኬብል  መዘጋጀት ይኖርበታል፤

8) የተሽከርካሪውን የእሳት አደጋ ደህንነት ለማረጋገጥ አሽከርካሪዎች የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስልጠና መውሰድ ይኖርበታል

9) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በተሽከርካሪው ላይ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

10) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው ሾፌር ሊኖረው ይገባል፤

11) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተሽከርካሪው ላይ መሟላት አለበት፤

12) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

13) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

## 8. የጋስ ማከማቻ ዴፖ የደህንነት መስፈርት

1) ከአንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሜትሪክ ቶን በታች መያዝ አቅም ያላቸዉ አነስተኛ የጋስ ዴፖ ጋኖች ከዋናው አጥር ሰላሳ ሜትር ርቀት፣ በዙሪያው ከአጥሩ ዉጪ ከአምስት ሜትር ያላነሰ ርቀት ነጻ መንገድ ኖሮት ተገቢ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን ሊኖርው ይገባል፤

2) ከአንድ መቶ ሰላሳ አምስት እስከ ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሜትሪክ ቶን የመያዝ አቅም ያላቸዉ መካከለኛ የጋስ ዴፖ ከጋኖቹ ከሰላሳ አምስት ሜትር ባላነሰ ርቀት ዙሪያዉን በብሎኬት መታጠር ያለበት ሆኖ በቂ ፎም የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን ሊኖርው ይገባል፤

3) ከሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሜትሪክ ቶን በላይ የመያዝ አቅም ያላቸዉ ትላልቅ የጋስ ዲፖዎች ከጋኖቹ በስልሳ ሜትር ርቀት ላይ ዙሪያዉን በብሎኬት ሊታጠር የሚገባ ሆኖ በቂ ፎም የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን ሊኖርው ይገባል፤

4) የጋስ ማከማቻ ዴፖ ተከላና ጥገና ከአደጋ በተጠበቀ ሁኔታ በዘርፉ የሥራ ፍቃድና በቂ ዕዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች እንዲከናወን ማድረግ ይገባል፤

5) የቡታ ጋስ ማከማቻ ጋኖች በሚያዝላቸዉ የጊዜ ሰሌዳ ጥገናና በጋኑ ዉስጥ ያለዉን የጋስ መጠን በማቃጠል የማስወገድ ሥራ የሚከናወን ከሆነ በቅድሚያ ለኮሚሽኑ በማሳወቅ የእሳት አደጋ መቆጣጠር ተሽከርካሪ በስፍራዉ እንዲገኝ ማድረግ ይገባል፤

6) የቡታ ጋስ ማከማቻ ጋኖችን ለማስተከል እና በየጊዜዉ የጥገና ሥራ ለማከናወን ከኮሚሽኑ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ያላቸው ድርጅቶችን የመጠቀም ግዴታ አለባቸው፤

7) ጋሱ ካለዉ ፈጣን ተቀጣጣይ ባህሪይ አኳያ የጋን ተከላ ቦታ መረጣ ከእሳት ጋርግንኙነት ያላቸዉ ማንኛውም የሥራ ክፍሎች/አይነቶች ተገቢዉን ርቀት እንዲጠብቅና አደጋ ምላሽ አሰጣጥን ቅድመ ዝግጅት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፤

8) የጋስ ማከማቻ ጋን ተከላ ከተለያዩ ተቋማትና አካባቢዎች የሚኖረዉ ርቀት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ሠንጠረዥ ቁጥር አንድ መሰረት ይሆናል፤

9) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

10) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

11) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

12) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

13) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

14) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፤ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

15) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

16) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

17) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

18) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

19) የጋስ ማከማቻ ዴፖ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

20) የጋስ ማከማቻ ዴፖ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

21) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

22) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

23) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

24) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

25) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ  የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት፤

26) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 9. ጋስ ማከፋፈያ ቦታዎች የደህንነት መስፈርት

1) በጋስ ማከፋፈያ ስፍራ በምንም አይነት ሁኔታ ከጋስ ሲሊደር ወደ ሲሊደር መገልበጥ ወይም መሙላት የተከለከለ ነው፤

2) በጋስ ማከፋፈያ ክፍል ግንባታ ከመሬት በላይ ሆኖ ለታለመለት አላማ ብቻ የሚውል ሲሆን በተለያየ አቅጣጫ በቂ የአየር ምልስስ እንዲያገኝ ተደርጎ መገንባት ይኖርበታል፤

3) የቡታ ጋስ መያዥ ሲሊንደር ባዶም ሆነ ሙሉ ሆኖ ሲጓጓዝ እና በማከማቻ ክፍል ውስጥ ሲቀመጥ ቀጥ ብሎ መቆም ይኖርበታል፤

4) ሲሊደር በተከማቸበት ስፍራ ከ50 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በላይ ለሆነ ሙቀት መጋለጥ የለበትም፤

5) ጋስ በሚከማችበት ስፍራ ማንኛውንም አይነት ክፍት እሳት ማቀጣጠልና መጠቀም እንዲሁም ሲጃራ ማጨስ የተከለከለ ነው፤

6) በአነስተኛ ደረጃ የሚገኙ የቡታ ጋስ መያዣ ሲሊንደር ከተለያየ አቅጣጫ ሊጠበቅ ስለሚገባው ርቀት እና ለቡታ ጋስ የእሳት ቃጠሎ አደጋ መቆጣጠር ሥራ የሚያስፈልጉ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን በተመለከተ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ሠንጠረዥ ቁጥር ሁለት እና ሶስት በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፤

7) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

8) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

9) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

10) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

11) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

12) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

13) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

14) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

15) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

16) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዩር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

17) ጋስ ማከፋፈያ ቦታዎች ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

18) ጋስ ማከፋፈያ ቦታዎች የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

19) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

20) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

21) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

22) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

23) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

24) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 10. የንግድና የገበያ ማዕከላት የደህንነት መስፈርት

1) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

2) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

3) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

4) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

5) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

6) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

7) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

8) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

9) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

10) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

11) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

12) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

13) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

14) በህንጻው ውስጥ ወይም ውጭ የተገል,ጋዩን ቁጥር ያገናዘበ በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ሊኖረው ይገባል፣

15) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

16) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

17) እንደ የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ባህሪና የተቀጣጣይነት ደረጃ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር

መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

18) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

19) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

20) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

21) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ. አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ. ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

22) ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

23) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

24) በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

25) የንግድና የገበያ ማዕከላት ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

26) የንግድና የገበያ ማዕከላት የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

27) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

28) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

29) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

30) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

31) የተገለጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

32) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

33) ግንባታዉን ከመኖሪያ አካባቢዎች በ50 ሜትር ርቀት ላይ ማከናወን ይገባል፤

34) የተለያዩ የሥራ ባህሪይ ያላቸዉን ሥራዎች ወይም ከንግዱ የሥራ ዘርፍ ጋር አብሮ የማይሄድ ንግድ ስራ በአንድ ላይ መከናወን የለበትም፤

35) በሱቆቹ መካከል ከ1 ሜትር ያላነሰ መተላለፊያ መንገድ ማዘጋጀትና በደህንነት ምልክቶች አማካኝነት ማመላከት አለበት፤

# 11. የአደገኛ ኬሚካሎችና ዉህዶች ደህንነት መስፈርት

1) በቀላሉ የእሳት ቃጠሎንም ሆነ አካባቢን የሚበክሉ ኬሚካሎች በመኖሪያ፣ ሆስፒታሎች፣ በትምህርት ተቋማት፣ በቢሮ ህንጻዎች፣ በገበያ ቦታዎችና አዳራሾች በቅርብ ርቀት ላይ ማከማቸት ፈጽሞ የተከለከለ ነዉ፤

2) የኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖቹ እሳትን ከሁለት ሰዓት በላይ መቋቋም የሚችሉና በኬሚካል ፍንዳታ ምክንያት በቀላሉ እንዳይፈርሱ ሆነዉ በኮንክሪት የተገነቡ በቂ የአየር ምልልስ ያላቸው መሆን ይኖርበታል፤

3) ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳያገኙ የተለያዩ ኬሚካልን ማከማቸት፣ መጠቀም ፣ ከቦታ ቦታ ማጓጓዝ እና ማስወገድ የተከለከለ ነው፤

4) በልዩ ሁኔታ ወይም የተለየ ፍቃድና መመዘኛ ካልተሰጠ በስተቀር የአደገኛ ኬሚካሎች ክምችት፣ አያያዝና አጠቃቀም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው አሰራር መሰረት መከናወን ይኖርበታል፤

5) ማናቸዉም ኬሚካል ወደ ማምረቻ ክፍል ዉስጥ የሚገባዉ ለዕለት ስራ የሚበቃዉን ያህል ብቻ ተመጥኖ መሆን አለበት፤

6) የሴሉሎስ ናይትሬት ፕላስቲክ (ፓይሮክሲሊን) የሚከማቸው ከእንፋሎት ቧንቧዎች፣ ራዲያተሮች፣ የጭስ ማውጫዎች፣ ምድጃዎች፣ መብራቶች፣ ቅርፅ ማውጫዎች፣ ነበልባል እሳት ወይም ኤሌክትሪክ ወይም ተመሳሳይ ብልጭታ ሊፈጥሩ የሚችሉ እሳት አመንጪ

መሳሪያዎች ከአንድ ሜትር በላይ ርቀት ባለው ለራሱ በተዘጋጀ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለበት፤

7) የሴሉሎስ ናይትሬት ፕላስቲክ በመጠቀም በፋብሪካ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ቢያንስ አንድ ሜትር ርቀት ላይ መሆን ያለባቸው ሲሆን ለአንድ ሰራተኛ የሚሰጠው ኬሚካል መጠንም ለግማሽ ቀን ከሚያስፈልገው መብለጥ የለበትም፣

8) አደገኛ የሆኑ ዝቃጭ ኬሚካሎች፣ እንደብረት ፍቅፋቂ፣ ቁርጥራጭ፣ ብናኝ የመሳሰሉ ማንኛውም የማይፈለጉ የሴሉሎስ ናይትሬት ውዳቂዎች ውሃ በተደረገበት የብረት ማጠራቀሚያ ውስጥ ከገቢው እስከሚወገዱ ድረስ ለደህንነት አስጊ ባልሆኑ ነጻ ስፍራዎች ላይ መከማቸት አለባቸው፤

9) ድንገተኛ ፍንዳታ የሚያስከትል ውህደት የሚያካሂዱ ወይም ሙቀት በማመንጨት የእሳት አደጋን የሚያስከትሉ ተቀጣጣይ ፈሳሾች እና በጠጣርነት መልክ የሚገኙ ኬሚካሎች በኮንክሪት በተገነባ ክፍል ዉስጥ በማከማቸት መጠቀም ያስፈልጋል፤

10)አደገኛ ኬሚካሎችን በመኖሪያ ህንጻዎች እና ለቢሮ አገልግሎት በሚዉሉ ህንጻዎች ዉስጥ ማከማቸትና መጠቀም ፈጽሞ የተከለከለ ነዉ፤

11)የኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች በሮች ከዉስጥ ወደ ዉጪ ተገፍተዉ ወይም ወደጎን ተንሸራተዉ የሚከፈቱ እና እሳትን ለሁለት ሰዓት መቋቋም የሚችሉ ሊሆኑ ይገባል፤

12)በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

13)በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

14)አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

15)በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

16)በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

17)ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

18)የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

19)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

20)ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

21)ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዩር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

22)የአደገኛ ኬሚካሎችና ዉህዶች ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

23)የአደገኛ ኬሚካሎችና ዉህዶች የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

24)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

25)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

26)የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

27)በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

28)የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

29)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 12. በመጋዘኖች ዉስጥ መሟላት እና መፈጸም ያለባቸዉ የደህንነት መስፈርት

1) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

2) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

3) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

4) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

5) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

6) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

7) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

8) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

9) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

10) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

11) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

12) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

13) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

14)በህንጻው ውስጥ ወይም ውጭ የተገልጋዩን ቁጥር ያገናዘበ በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ሊኖረው ይገባል፣

15)በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

16)በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

17)እንደ የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ባህሪና የተቀጣጣይነት ደረጃ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ እስከ 150 ሺ ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፐሊንግ መገጠም አለበት፤

18)ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

19)የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

20)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

21)ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

22)ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

23)ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

24)በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

25)በመጋዘኖች ዉስጥ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

26)በመጋዘኖች ዉስጥ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

27)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

28)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

29)የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

30)በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

31)የተገለጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ  የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

32)በማንኛዉም የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ዕቃዎች አደራደር እንደዓይነታቸዉና በቃጠሎ አደጋ ጊዜ በሚኖራቸዉ የመቀጣጠል ባህሪ ላይ ተመስርቶ ከጣራዉ አንድ ሜትር፣ ከግድግዳ ግማሽ ሜትር እንደዚሁም በእያንዳንዱ ድርድር መካከል አንድ ሜትር መተላለፊያ ርቀት በመጠበቅ መደርደር አለበት፤

33)የማከማቻ መጋዘኑ ግንባታ ስፋትና የእቃዎች ተቀጣጣይነት ባህሪ ግምት ውስጥ ያስገባ ፤ ሁለትና ከሁለት በላይ በር በተለያየ አቅጣጫ ያለው ፤ ከመኖሪያ አካባቢ፣ ከጋራዥና ከተለያዩ ድርጅቶች ቢያንስ 50 ሜትር የራቀና  እሳትን  ለተወሰነ  ሰዓት  ሊቋቋሙ ከሚችሉ  ከድንጋይ፣ ከሸክላ፣ ከብሎኬት ወይም በኮንክሪት መገንባት ይኖርበታል፣

34) የአደጋ ጊዜ ማምለጫ በሮች አሰራራቸዉ ከዉስጥ ወደ ዉጪ ሲገፉ የሚከፈቱ ወይም ወደጎን የሚንሸራተቱ ሆነው አካባቢ ያለዉ ዉጫዊ መንገድ የወለል አሰራሩ ከቤቱ ወለል ጋር እኩል የሆኑ የአደጋ ጊዜ መዉጫ የሚል ምልክት በአንጸባራቂ ፅሁፍ ወይም በስዕላዊ መግለጫ የተመላከቱ   መሆን አለባቸው፤

35)በመጋዘኑ በተለይም ውስጣዊ ግድግዳ ዙሪያ እና ጣሪያ ላይ ምንም ብናኝ ሆነ ሌሎች የእሳት ቃጠሎ አደጋን ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን በማፅዳት አደጋን መከላከል ይገባል፤

36)የመጋዘኑ ጣሪያ አሰራር ቢያንስ መጠኑ ከአንድ መቶ ሃያ ሴንቲ ሜትር ያላነሰ የከፍታ ይዘት እንዲኖረው በማድረግ በግድግዳዉ ዙሪያ በየ ሃያ ሦስት ሜትር ርቀት ላይ በመስኮት መልክ የማናፈሻ መስመር መዘጋጀት ያለበት ሆኖ መጋዘኑ በግድግዳ

የሚከፋፈል ከሆነ የግንባታው ግብዓት እሳትን ቢያንስ ለሰላሳ ደቂቃ መቋቋም የሚችሉ መሆን አለበት፤

37)የማግኒዚየም ዱቄት መከማቸት ያለበት በብረት ድራም ወይም ሌላ ዓይነት ዝግ መያዣ ዉስጥ መሆን ያለበት ሲሆን መያዣዎቹም በጥብቅ ታሽገዉ በደረቅ ስፍራ ላይ መከማቸት አለባቸዉ፤

38)ተቀጣጣይ የሆኑ ፈሳሽ ነገሮች ባላቸዉ የመቀጣጠል ባህሪያቸው ደረጃ ተለያይተው በመያዥነት በሚያገለግለው እቃ ላይ በጽሁፍ ወይም ስዕላዊ መግለጫ ተደርጉላቸው መከማቸት አለባቸው፤

39)ተቀጣጣይ የሆኑ ፈሳሾች ተንቀሳቃሽ በሆኑ መያዥ ሲዘጋጁ በመዉጫ ደረጃዎች አጠገብ ወይም በመደበኛነት በመግቢያነትና በመዉጫነት በሚያገለግሉ በሮች አካባቢ መከማቸት የለባቸዉም፤

40)ማንኛውም የፈሳሽ መያዣ ሲከማች ቀጥ ብሎ መሆን ያለበት ሲሆን የመያዝ አቅማቸዉ ከአንድ መቶ አስራ ሦስት ሊትር በላይ ድራም ወይም መያዣ ተደራርበዉ መቀመጥ የለባቸዉም፤

41)በመደርደሪያ ላይ የሚደረደሩት ዕቃዎች የመደርደሪያ አሰራሩ በቂ ጥልቀት ባለዉና በመደርደሪዉ ዉስጥ የሚታዩ መያዣዎች ቦታቸዉን በቀላሉ ሊለቁ በማይችሉበት የተጠናከረ ሁኔታ የተሰራ መሆን አለበት፤

42)የሚያንጠባጥብ የፈሻስ ነዳጅና ተቀጣጣይ ኬሚካል መያዥ እቃ ከክፍት እሳት ወይም ከብልጭታ መጠበቅና አካባበው በቶሎ መፅዳት ይገባዋል፤

43)የማከማቻ መጋዘኑ መተላለፊያ መንገድ ቢያንስ 2.4 ሜትር ስፋት ያለው ወይም ተሽከርካሪ ፎርክሊፍት ማስተላለፍ የሚያስችል ስፋት ሊኖረዉ ይገባል፤

44)ተቀጣጣይ ፈሳሾች የተከማቹት በመደርደሪያ ላይ ከሆነ ጎን ለጎን ባሉ መደርደሪያዎች መካከል ቢያንስ የ1.2 ሜትር ስፋት ያለዉ መተላለፊያ ሊኖረው ይገባል፤

45)በአየር ንብረት መለዋወጥ ምክንያት የኬሚካል ክምችቱ አደጋ እንዳያደርስ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግና በአቅራቢያው ከሚገኝ ማንኛውም ነገር ከ15-18 ሜትር ርቀት በላይ በመራቅና ከተፈቀደለት ውጭ ከሰውና እንስሳት ንኪኪ የፀዳ መሆን ይገባዋል፤

46)መጋዘኖችን ጸረ ተባይ ኬሚካልና ሌሎች የማጠን ሥራ ከተከናወነ በኃላ ሰዎች ወደ መጋዘኑ እንዲገቡ ለማድረግ የተረጨው ኬሚካል ትነት በሰዉ ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

47)ማንኛዉም የማጠንም ሆነ የፀረ ተባይ ኬሚካል ርጭት በባለሙያ ሲከናወን በአካባቢዉ ምንም ዓይነት ከእሳት ጋር የተገናኘ ሥራ መከናወን የለበትም፤

## 13. የትርኢት፣ ሲኒማ፣ ኤግዚቢሽን ማሳያ፣ የመሰብሰቢያና የሙዚቃ ማዘጋጃ አዳራሽ የደህንነት መስፈርት

1) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

2) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

3) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

4) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

5) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

6) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

7) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

8) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

9) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

10) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

11) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረገ ይገባል፤

12) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

13) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

14) በህንጻው ውስጥ ወይም ውጭ የተገልጋዩን ቁጥር ያገናዘበ በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ሊኖረው ይገባል፣

15) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

16) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

17) እንደ የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ባህሪና የተቀጣጣይነት ደረጃ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ እስከ 150 ሺ ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

18) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

19) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

20) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

21) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

22) ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

23) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

24) በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

25) የትርኢት፣ ሲኒማ፣ ኤግዚቢሽን ማሳያ፣ የመሰብሰቢያና የሙዚቃ ማዘጋጃ አዳራሽ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

26) የትርኢት፣ ሲኒማ፣ ኤግዚቢሽን ማሳያ፣ የመሰብሰቢያና የሙዚቃ ማዘጋጃ አዳራሽ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

27) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

28) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

29) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

30) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

31) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

32) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

33) ለትርኢት፣ ለሲኒማ፣ ኤግዚቢሽን ማሳያ፣ ለመሰብሰቢያ ቦታና ለሙዚቃ ማዘጋጃ የሚገነባ ህንጻ፡-

ሀ/ እሳትን ከ1 ሰዓት በላይ የሚቋቋም እና የቤቱ ግድግዳ ደረጃ በደረጃ ከፍታው የሚለያይ ካልሆነ በስተቀር ቁመቱ ከ4-6 ሜትር ያ ላ ነ ሰ

ለ/ አውቶማቲክ የሆነ የአየር ማመጣጠኛ/ማስተካከያ ስርዓት ያለው ፤

ሐ/ ኮርኒሱ ድምጽ ወደ ውጭ የማያስወጣና እሳትን ቢያንስ ከ30 ደቂቃ ላላነሰ ጊዜ መቋቋም የሚችል መሆን አለበት፤

34.በኤግዚብሽን ማዕከላት ለእይታ የሚቀርቡ እቃዎች ሲደረደሩ/ሲቀመጡ/ የደህንነት መስፈርትን ጠብቀው መሆን አለበት፤

35. በጊዚያዊነት የሚዘጋጁ የኢግዚቢሽኑ ማሳያ ቦታዎች ከአንድ ሳምንት በፊት በኮሚሽን መ/ቤቱ ጊዜያዊ ፈቃድ ማግኘትና የተመልካቹን ደህንነት ትርዒቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ የማስጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፤

36. በትርኢት ማሳያው መድረክና ከመድረክ ጀርባ ላይ የሚገጠሙ የትእይንት መከለያ መጋረጃና የወለል ምንጣፍ እሳት ቢያንስ ለ30 ደቂቃ የሚቋቋሙ መሆን አለባቸው፤

37. የቲያትር፣ ሲኒማ፣ የመሰብሰቢያና ትርኢት ማሳያ አዳራሽ መቀመጫዎች፡-

ሀ/ የማይንቀሳቀሱ ሆነው ስፋታቻው ከ450 ሚ.ሜ ቁመቱ ከ550 ሚ.ሜ ያላነሰ፤

ለ/ በየድርድሩ መሀከል ያለው ክፍተት ከ360 ሚ.ሜ ያላነሰ፤

ሐ/ ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላ ጫፍ የሚዘረጋው ብዛት 14 ሆኖ ባለ አንድ አቅጣጫ መተላለፊያ ከሆነ ከ7 የማይበልጥ፤

መ/ በመደዳ ከ15-18 ከሆኑ በየድርድሩ መሀከል ያለው ክፍተት ከ400 ሚ.ሜ ያላነሰ፤

ሠ/ በመደዳ ከ19-35 ከሆኑ በየድርድሩ መሀከል ያለው ክፍተት ከ450 ሚ.ሜ ያላነሰ እና በ14 ወንበር መሀከል ከ1 ሜትር ያላነሰ ክፍተት ሊኖር ይገባል፤

ረ/ በረድፍ ከ36-45 ከሆነ በየድርድሩ መሀከል ያለው ክፍተት ከ500 ሚ.ሜ ያላነሰ እና በየ 14 ወንበሮች መሀከል 1ሜትር ክፍተት እንዲኖረው ተደርጎ ሁለት ቦታ ላይ ለ1ሜትር ስፋት ያለው መተላለፊያ ሊኖረው ይገባል፤

ሰ/ በረድፍ ከ46-100 ከሆነ በየድርድሩ መሀከል ከ550 ሚ.ሜ ያላነሰ ያለው ሆኖ በየ14 ወንበሮች መሀከል ባለ1 ሜትር ስፋት ያለው መተላለፊያ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

ሸ/ በረድፍ ከ100 በላይ ድርድር የሚዘጋጅ ከሆነ በባለሙያዎች መወሰን ይኖርበታል፤

## 14. የኢንዱስትሪና ኢንዱስትሪ ነክ ድርጅት የደህንነት መስፈርት

1) በኢንዱስትሪዉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቢያንስ አንድና እንደ የኢንዱስትሪዉ ስፋት በተጨማሪ በየ ሃምሳ ሜትር ርቀት ላይ አንዳንድ ፒላር ፋየር ሃይድራን ከተሟላ መሳሪያ ጋር መዘጋጀት አለበት፤

2) ኢንዱስትሪው ለእለቱ ከሚያስፈልገው የምርት ሥራ በስተቀር ምንም አይነት ጥሬ እቃም ሆነ ምርት በማምረቻ ክፍል ውሰጥ መከማቸት የለበትም፤

3) በኢንደስትሪ በጥሬ እቃነት ወይም በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቀ ምርት የስራ አካባቢ ደህንነትን በጠበቀ ሁኔታ መከማቸት፣ መወገድ ወይም ለገበያ መቅረብ ይኖርበታል፤

4) የፈርኒቸርና የጣውላ መሰንጠቂያዎች በህንጻ ውስጥ ወይም ክምችቱ ከህንጻ ውጭ ሲሆን ከ1.8-2 ሜትር ከፍታ ባለው አጥር ክልል ውስጥ መሆን ይኖርበታል፤

5) በማምረቻ ክፍል ጣውላ ሲከማች የክምችቱ ከፍታ በአካባቢው ለሥራ በሚንቀሳቀሱ ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ቁመቱ ከ3 ሜትር መብለጥ አይኖርበትም፣

6) የእንጨቱ ልጣጭ፣ ፍቅፋቂ፣ ሰጋቱራ በየቀኑ መወገድ ያለባቸው ሲሆን በማቃጠል የሚወገድ ከሆነ ለዚሁ ስራ በተዘጋጀ ስፍራ በአካባቢው አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎች ከተሟሉ በኋላ መከናወን አለበት፤

7) ማንኛውም ኢንዱስትሪ በአደጋ ጊዜ የመውጫ አቅጣጫው የመጨረሻ መውጫ ላይ ከስድሰት ሜትር የማይበልጥ ተጨማሪ ቅጥያ ሊኖር ይገባል፤

8) በከፍተኛ ኢንደስትሪ እንደ አውሮፕላን መገጣጠሚያ፣ ከፍተኛ የብረት ውጤቶች ማምረቻ፣ ከፍተኛ ወርክ ሾፖች ያሉበት ከምድር በታች የሚገኑ ወለሎች አመቺ መውጫ በማይኖርበት ወቅት ወደ መውጫ የሚያመሩ መንገዶችን በተመለከተ የሚከተለውን ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ/ በኢንዱስትሪ ህንጻ ውስጥ የመውጫ በር ድረስ የሚገኘው ርቀት በምንም አይነት ሁኔታ ከዘጠኝ ሜትር ያልበለጠ ሆኖ የስራ ቦታው ባለአንድ ወለል ሲሆን አውቶማቲክ ለእሳት መቆጣጠሪያ የሚሆን ስፕሪንክለር መገጠም አለበት፤

ለ/ በኢንዱስትሪ ህንጻ ወርክሾፖች ውስጥ ቢያንስ ከሁለት ያላነስ መውጫ በር ሊኖረው ይገባል፤

ሐ/ የተጠቃሚዎች ብዛት ከ25 ሰዎች የማይበልጥ ሆኖ በምድብ 2 ለተመደበ ኢንደስትሪ ነክ ህንጻ ከመሬት በላይ ወይም በአቅራቢያው በሚገኝ ወለል ውስጥ ከሚገኝ ማንኛውም ነጥብ የውጭ ግድግዳ ውስጥ እስከሚገኘው በር ድረስ ሊኖር የሚገባው ርቀት ከ15 ሜትር ያላነሰ ሲሆን አንድ መውጫ መስመር ያስፈልጋል፤

መ/ በኢንዱስትሪ ህንፃ ውስጥ የሰዎች ብዛት ከ100 በላይ ከሆነ ወይም ከመልቀቂያ ወለል በላይ ወይም በታች ያለው ቦታ የሚይዘው ከ25 ሰዎች በላይ ከሆነ በእያንዳንዱ ወለል መልቀቂያ እና የአሳንሰር መዳረሻ አካባቢ በአደጋ ጊዜ የማንቂያ ደወል መገጠም አለበት፤

ሠ/ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከእሳት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ክፍሎች ማለትም ቦይለር፣ ኮምፕረሰር፣ ምድጃ፣ ማቅለጫ፣ መቀቀያ የመሳሰሉ ክፍሎች እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ሊደረግላቸውና ከሌሎች ክፍሎች የህንጻ አካላት እሳትን በከፍተኛ ደረጃ መቋቋም የሚያስችል ይዘት እንዲኖራቸው መደረግ አለበት፤

9) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

10) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

11) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትሪክ ደረጃውን የጠበቀ ፣ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

12) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

13) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

14) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

15) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

16) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

17) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

18) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

19) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

20) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

21) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

22) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

23) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

24) እንደ የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ባህሪና የተቀጣጣይነት ደረጃ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

25) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

26) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

27)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

28) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

29) ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

30) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

31) በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

32) በእያንዳንዱ ድርጅት ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

33) እያንዳንዱ ድርጅት የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

34) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

35) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

36) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

37) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

38) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ  የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

39) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 15. ፈንጂዎች፣ ጥይቶች፣ ርችት እና መሰል መሳሪዎች ማከማቻ፣ ማሳያና መተኮሻ ስፍራ የደህንነት መስፈርት

1) ፈንጂና ፈንጂ ነክ ነገሮች መጠቀም፣ መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማምረት እና ማስወገድ የሚመለከተው ህግ ተከትሎ መከናወን አለበት፤

2) በመጋዘኖቹ ዙሪያ በአስራ አምስት ሜትር ርቀት ከማንኛውም ነገሮች ነጻና ምንም የንብረት ክምችት፣ የትራፊክ እንቅስቃሴና እሳትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ነገሮች እንዳይኖር የማድረግና አካባቢዉንም በጥንቃቄ መያዝ ይገባል፤

3) የዘርፉ ምርት ወደ ማከማቻው ሲገባ ወይም ሲወጣ ለተፈቀደለት ሰው ሲጎበኙ ካልሆነ በስተቀር ክፍት መሆን አይኖርባቸውም፤

4) ማከማቻ መጋዘኖቹ ውስጥ በባለሙያ ተጠንቶ እንዲኖር ከሚደረግ ሰው-ሰራሽ ሙቀትና ብርሃን በስተቀር ምንም አይነት የውጭ ብርሃን መግባት እና ከተገቢው በላይ ሙቀት መፈፀር የለበትም፤

5) ፈንጂውን ለማፈንዳትና ለማምከን የሚያገለግል ቁሳቁስ ከፈንጂዎቹ ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ መከማቸት የለበትም፤

6) የፈንጂ እሽግ መጋዘን ውስጥ ወይም መጋዘኖቹ ከሚገኙበት 50 ሜትር ርቀት ክልል ውስጥ ወይም ሌሎች ፈንጂ ነክ ነገሮች በቅርብ ርቀት በድጋሚ መታሸግ የለባቸውም፤ የተከፈተ የፈንጂ እሽግ ከመመለሱ በፊት በጥንቃቄ መዘጋት አለበት፤

7) የመጋዘኖች ወለል በመጋዘኑ ውስጥ በሚኖር የማቴሪያል ክብደቱን በሚሸከም አቅም ዲዛይን ተደርገው መገንባት ይኖርባቸዋል

8) በመጋዘኑ ውስጥ አላስፈልጊ የሚሆን ሙቀትና እርጥበት እንዳይኖር ወይም በቂ የአየር ምልልስ እንዲኖር መደረግ አለበት፤

9) ፈንጂ ነክ ነገሮች ለተፈለገው አገልግሎት በማንኛውም አካባቢ ጥቅም ላይ ከመዋላቸዉ በፊት ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ከ24 ሰዓት በፊት ማሳወቅ አለበት፤

10)የፍንዳታ ወይም የማምከን ስራ ከመከናወኑ በፊት የሰውና እንስሳት ንክኪ እንዲሁም በትርፍነት ከተያዙ ፈንጂዎች የራቀ ስለመሆኑ፣ ተንቀሳቃሽ የሬድዮ መገናኛ በ107 ሜትር ርቀት ክልል ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውል ስለመደረጉ፣ ሂደቱ በባለሙያ የታገዘ ስለመሆኑ፣ ከአጭር ሞገድ ሬድዮ ማስተላለፊያ በ2.5 ኪ.ሜ መራቁ እና ሌሎች መሰረተ ልማት ግንባታዎች ላይ ጉዳት አለማድረሱን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባትና መረጋገጥ እና ተገቢው ጥንቃቄ መውሰድ አለበት፤

11)የፈንጂ እሽጎችን ለመክፈቻነት የሚውሉ መሳሪያዎች ብልጭታ የማይፈጥሩ ዓይነት መሆን አለባቸው፤

12)ማንኛውም ፈንጂ ነክ ነገሮች የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ በቂ የጅምር የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ ሚሟላትና የመሰሪያዎቹ አቀማመጥ በቀላሉ ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ ማደራጀትእና ተሽከርካሪዉ በሁለቱም ጎን አደገኛ የሆነና የሚፈነዳ ማቴሪያል የጫነ ስለመሆኑ ጉልህ በሆነ ሁኔታ በአንጸባራቂ ስእል ወይም ጽሁፍ ማመልከት እነዲሁም ሁለትና ከዛ በላይ ተሽከርካሪዎች በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚጓዙ ከሆነ በመሀከል ከአንድ መቶ ሜትር ያላነሰ ርቀት መኖር አለበት፤

13)ይህን አይነት ጭነት የያዘ ተሽከርካሪ በማንኛውም ሰዓት በመኖሪያ አካባቢ፣ ህዝብ በብዛት በሚበዛባቸው አከባቢ ሲንቀሳቀስ ከፍተኛ ቁጥጥር መደረግ አለበት፣ ፈቃድ ያልተሰጠው ሰው በምንም አይነት ሁኔታ አብሮ መጓዝ አይፈቀድም፤

14)የርችቶች ተኩስ የሚካሄድበት ህጋዊ ሥፍራ በአካባቢው ከሚገኙ ሰዎች ሰላሳ ሦስት ሜትር እና በላይ በመራቅ በቀጥታ ወደ ሰማይ መከናወን አለበት እነዲሁም በትርኢቱ ሥፍራ ለሚገኝ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አስቀድሞ በማሳወቅ አንድ አደጋ ተሽከርካሪ ከበቂ አባሎች ጋር በስፍራው ላይ እንዲመደብ መደረግ አለበት፤

15)ያልተተኮሰ ርችት ትርኢቱ ከተጠናቀቀ በኃላ ከአካባቢዉ ተገቢ በሆነ የጥንቃቄ ስርዓት መወገድ አለበት፡፡

16)በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

17)በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

18)አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

19)በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

20)በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

21)ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

22)የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

23)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

24)ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

25) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

26)ፈንጂዎች፣ ጥይቶች፣ ርችት እና መሰል መሳሪያዎች ማከማቻ፣ ማሳያና መተኮሻ ስፍራ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

27)ፈንጂዎች፣ ጥይቶች፣ ርችት እና መሰል መሳሪያዎች ማከማቻ፣ ማሳያና መተኮሻ ስፍራ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

28)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

29)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

30)የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

31)በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

32)የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ  የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

33)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 16. የከፍተኛ ደረጃ ሆቴሎች ደህንነት መስፈርት

1) የእሳት ቃጠሎ አደጋ መቆጣጠሪያ የሚሆን ከአንድ መቶ ሃምሳ ሜትር ኪቢክ ያላነሰ በቂ ውሃ ክምችት፤ በደቂቃ 2000-2500 ሊትር ውሃ መግፋት የሚችል ፋየር ፓምፕ እና በእያንዳንዱ ፋየር ፖይንት ላይ የውሃው ግፊት ከ10 ባር ያላነሰ መኖር ይገባዋል፤

2) በአደጋ ጊዜ የመውጫ አቅጣጫው በኩል የሚኖረው ርቀት ከ30 ሜትር ያልበለጠ ፣ ጭስ የማያሳልፍ፣ እሳት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል በር መገጠም፣ በእያንዳንዱ የእንግዳ ማረፊያ ኮሪደር ላይ በአደጋ ጊዜ ሰዎችን ማንቂያ የሚሆን ድምጽ ማጉያ መገጠም አለበት፤

3) በሆቴሉ አጠቃላይ የአደጋ ስጋት ደህንነት እንቅስቃሴን የሚቆጣጣር ኮምፒውተራይዝድ ስርዓት (control panel board) በአንድ ማእከላዊ ስፍራ ላይ መዘጋጀት አለበት፤

4) የቡታጋስ ሲሊንደሮችን ከማብሰያ ክፍሉ ዉጪ በማድረግ ተገቢ የእሳት ማጥፊያ ማሳሪያና የጋስ ሊንኬጅ መኖሩን የሚያሳዉቅ የጋስ አነፍናፊ እንዲዘጋጅላቸዉ መደረግ አለበት፤

5) የከፍተኛ ደረጃ ሆቴሎች ባህሪና የተቀጣጣይነት ደረጃ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ፋየር ሀይድራንት መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ   ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

6) በእያንዳንዱ የእንግዳ ማረፊያ ክፍልና ኮሪደር እንዲሁም የእንግዳ መቀበያ ሥፍራ አዉቶማቲክ የዉሃ መርጫ ሲስተም /sprinkler system/ መገጠም አለበት፤

7) በእንግዳ ማረፊያ ክፍሎች፣ ኮሪደሮች እና ቢሮዎች ላይ ለእንግዶችና ሰራተኞች ቅስቀሳና መረጃ ለመስጠት የሚያስችል የድምፅ ማጉያ መሳሪያ /Public addressable/ መዘጋጀት አለበት፤

8) በጋሪ ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት /Ramp/ መገጠም ይኖርበታል እንዲሁም በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ዊልቸር ወይም ኢቫክ ቸር (Evac chair) መዘጋጀት አለበት፤

9) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

10)በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

11) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

12) የከፍተኛ ደረጃ ሆቴሎች ዉስጥ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

13) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

14) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

15) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

16) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

17) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

18) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

19) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

20) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

21)በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

22) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

23) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

24) የከፍተኛ ደረጃ ሆቴሎች ዉስጥ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፣

25) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

26) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

27) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

28) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

29)ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

30) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

31)በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

32) የከፍተኛ ደረጃ ሆቴሎች ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

33) የከፍተኛ ደረጃ ሆቴሎች የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

34) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

35) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

36) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

37) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

38)የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

39) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 17. የመካከለኛ ደረጃ ሆቴሎች አደጋ ስጋት ደህንነት መስፈርት

1) የእሳት ቃጠሎ አደጋ መቆጣጠሪያ የሚሆን ከ115 ሜትር ኪቢክ ያላነሰ በቂ ውሃ ክምችት፣ በደቂቃ 2000-2500 ሊትር ውሃ መግፋት የሚችል ፋየር ፓምፕ እና በእያንዳንዱ ፋየር ፖይንት ላይ የውሃው ግፊት ከ8 ባር ያላነሰ መኖር ይገባዋል፤

2) በአደጋ ጊዜ የመውጫ አቅጣጫው በኩል የሚኖረው ርቀት ከ30 ሜትር ያልበለጠ ፣ ጭስ የማያሳልፍ እና እሳት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል በር መገጠም አለበት፤

3) በሆቴሉ አጠቃላይ የአደጋ ስጋት ደህንነት እንቅስቃሴን የሚቆጣጠር ኮምፒውተራይዝድ ስርዓት (control panel board) በአንድ ማእከላዊ ስፍራ ላይ መዘጋጀት አለበት፤

4) የቡታጋስ ሲሊንደሮችን ከማብሰያ ክፍሉ ዉጪ በማድረግ ተገቢ የእሳት ማጥፊያ ማሳሪያ መዘጋጀት አለበት፡፡

5) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

6) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለአንድ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

7) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

8) የመካከለኛ ደረጃ ሆቴሎች ህንጻ ዉስጥ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

9) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

10) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

11)የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

12)የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

13)የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

14) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

15) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

16) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

17) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

18) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

19) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

20) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፣ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

21) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

22) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

23) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

24)ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ሆኖ የቢሮ ህንፃ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

25) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

26) በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

27)የመካከለኛ ደረጃ ሆቴሎች ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

28) የመካከለኛ ደረጃ ሆቴሎች የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

29) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

30) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

31) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

32)በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

33) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት፤

34)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 18. የዝቅተኛ ደረጃ ሆቴሎች አደጋ ስጋት ደህንነት መስፈርት

1) የቡታ ጋስ ሲሊንደሮችን ከማብሰያ ክፍሉ ዉጪ በማድረግ ተገቢ የእሳት ማጥፊያ ማሳሪያ መዘጋጀት አለበት፤

2) በጋሪ ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት /Ramp/ መገጠም ይኖርበታል እንዲሁም በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ዊልቸር መዘጋጀት አለበት፤

3) የሆቴሉ ህንጻ በምድብ ሁለት ውስጥ የሚመደብ ከሆነ ተጨማሪ አንድ በአደጋ ጊዜ መውጫነት የሚያገለግል ደረጃ ማሟላት ይገባል፤

4) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

5) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

6) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

7) የዝቅተኛ ደረጃ ሆቴሎች ህንጻ ዉስጥ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

8) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

9) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

10) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

11) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

12) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

13)በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

14) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

15) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

16)በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

17) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

18) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፣

19) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፣

20) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

21) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

22) ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

23) በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

24) የዝቅተኛ ደረጃ ሆቴሎች ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

25) የዝቅተኛ ደረጃ ሆቴሎች የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

26) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

27) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

28) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

29) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

30) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

31) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 19. የሆስፒታል፣ ጤና ማእከልና ጤና ጣቢያዎች የደህንነት መስፈርት

1) የህክምና ማዕከላት ወይም እንክብካቤና ድጋፍ የሚያገለግሉ ህንጻዎች ውስጥ የእሳት ቃጠሎ አደጋ ቢከሰት ታካሚዎችን በሙሉ እንዲወጡ የሚያስችል እንዲሆን ተደርገው አስቀድሞ የዲዛይን ስራቸው መዘጋጀት አለበት፣

2) የሥነ-ልቦና ወይም የአዕምሮ ህሙማን በሚታከሙበት ህንጻ ውስጥ የሚገኙ በሮች አውቶማቲክ ወይም ማንዋል በሆነ አሰራር የሚከፈቱና የሚዘጉ መሆን አለባቸው፣ በቁልፍ የሚቆለፉ ከሆነ ቁልፉ በአስታማሚዎቻቸው ወይንም በሚመለከተው አካል እጅ መገኘት አለበት፣

3) በጤና ተቋሙ በተለይ የተካሚዎች ማቆያ፣ የማወላጃ እና የቀዶ ህክምና ክፍል በሚገኙበት ወለል ላይ የሚገኙ በሮች በራሳቸው ጊዜ የሚዘጉና ጭስ የማያሳልፉ፣ ሙቀትና ነበልባልን ቢያንስ ከ30 ደቂቃ በላይ መቋቋም የሚችሉ መሆን አለባቸው፣

4) በጤና ተቋሙ ውስጥ በዊልቸር ለሚንቀሳቀሱ ተገልጋዩች ሊጠቀሙበት የሚያስችል በተቋሙ መግቢያና መውጫ ተዳፋት መንገድ መኖር አለበት፣

5) ማንኛውም 90 ሜ.ካ ስፋት ያለው የጤና ተቋሙ ክፍል ቢያንስ ሁለት ወደ ውጭ የሚያስወጣ በር ሊኖረው ይገባል፣

6) ጨረር ሊያመነጩ የሚችሉ መሳሪያዎች የሚገኙባቸው የኤክስሬይ እና ራዲዮሎጂ ክፍሎች በአካባቢው ባሉ ተገልጋዩች ላይ ጨረሩ ጉዳት እንዳያደርስ የዲዛይን ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዘጋጅ ይገባል፣

7) የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት ህንጻ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ በደቂቃ 2000 ሊትር መርጨት የሚችል ፋየር ፓምፕ፣ ከ113 ሜትር ኪዩቢክ ያላነሰ የውሃ ክምችት ከስፕሪንክለር ሲስተም እና የውሀ ግፊት ከ7.5 ባር መጠን ያላነሰአብሮ መዘጋጀት አለበት፣

8) በታካሚዎች መኝታ ክፍል ውስጥ በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ የአየር ማሞቂያ መሳሪያ መጠቀም የተከለከለ ነው፣

9) የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሀኒቶችንና መሳሪያዎችን በማቃጠል የማስወገድ ስራ የመንግስት ተቋም ፈቃድ ሲገኝና የአካባቢ ጥበቃና ደህንነት መስፈርትን ሲያሟላ በተዘጋጀው የተከለለ ማቃጠያ ስፍራ መወገድ አለበት፣

10) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፣

11) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፣

12)በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

13)ለሆስፒታል፤ ጤና ማእከልና ጤና ጣቢያነት አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

14)በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

15)በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

16)የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

17)የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

18)የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

19)በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

20)በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

21)አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

22)በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

23)በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

24)በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

25)ለሆስፒታል፣ ጤና ማእከልና ጤና ጣቢያነት አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

26)ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፣ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

27)የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

28)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

29)ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

30)ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

31)ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

32)በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

33)ለሆስፒታል፣ ጤና ማእከልና ጤና ጣቢያነት አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

34)ለሆስፒታል፣ ጤና ማእከልና ጤና ጣቢያነት አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

35)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

36)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

37)የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

38)በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

39)የተገለጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት፤

40)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 20. የማረሚያ ቤት የደህንነት መስፈርት

1) ለ ማረሚያ አገልግሎት ተደራራቢ ወለል ያላቸው ህንጻዎች የሚገነቡ ከሆነ በእያንዳንዱ ህንጻ ላይ ቢያንስ በተለያየ አቅጣጫ ላይ የተገጠመና ወደ መውጫዎቹ ለመድረስ የሚደረገው ጉዞ ከ30 ሜትር የማይበጥ መሆን አለበት፤

2) የመኝታ ክፍሎቹ በቀጥታ ከቀን መዋያ ወይም ወደ ውጭ ለመውጣት የሚያገለግሉ የቡድን እንቅሰቀሴ ስፍራዎች ጋር በቀጥታ የተያያዘ ከሆነ የመኝታ ክፍሉ ወደ ቀን መዋያ በቀጥታ ክፍት እንዲሆኑ ይፈቀዳል፣ ወደ መውጫዎች የሚደረግ ጉዞ ርቀት፡-

   ሀ/ መውጫ መዳረሻ እንዲሆን ከታሰበ የማንኛውም ክፍል በር እና በመውጫው መካከል ያለው ርቀት ከ 30 ሜትር መብለጥ የለበትም፤

   ለ/ በማንኛውም ክፍል ውስጥ ያለ ስፍራ እና በመውጫው መካከል ያለው ርቀት ከ46 ሜትር መብለጥ የለበትም፤

   ሐ/ ከማንኛውም መኝታ ክፍል ውስጥ ካለው ሥፍራ እስከ ክፍሉ በር ድረስ የሚኖረው ከፍተኛ የጉዞ ርቀት ከ 10 ሜትር መብለጥ የለበትም፤

   መ/ በዚህ ስፍራ የሚገኙ የታራሚዎች መኖሪያ ክፍሎች ግንባታ ለአንድ ሰዓት እሳትን የመቋቋቀም አቅም ሊኖረው ይገባል፤

3) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

4) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለአንድ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

5) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፣ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

6) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

7) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

8) በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

9) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

10)የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

11) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

12) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

13) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

14) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

15) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

16) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

17) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

18) የማረሚያ ቤት  ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

19) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

20) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሸከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

21) የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

22) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

23) ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

24) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

25) በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

26) የማረሚያ ቤት  ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

27) እያንዳንዱ ድርጅት የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

28) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

29) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

30) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

31) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

32) የተገለጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

33) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 21. የቴሌ ኮሙኒኬሽን ተቋማት፣ የሬድዮና ቴሌቪዥን ማሰራጭያ ጣቢያዎች የደህንነት መስፈርት

1) ቴሌ ኮሙኒኬሽን ተቋማት እና ሬድዮና ቴሌቪዥን ማሰራጭያ ጣቢያ ፡-

ሀ/ ህንጻው እሳትን 2 ሰዓት ያህል የመቋቋም አቅም ሊኖረው ይገባል፤

ለ/ የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ሲሆን በተለያየ አቅጣጫ ላይ የተገነባ በአደጋ ጊዜ መውጫ የሚሆን ደረጃ መገጠም አለበት፤

ሐ/ በእያንዳንዱ የሥራ ክፍልና ኮሪደር ላይ አደጋን ገና በጅምር ደረጃ ላይ እንዳለ የሚጠቁም መሳሪያ መገጠም አለበት፤

መ/ በእያንዳንዱ የቴክኒክ ክፍልና የተለያዩ ቦታዎች ላይ በአደጋ ጊዜ የማንቂያ ደወል መገጠም አለበት፤

ሠ/ ያላቸውን አደጋን የመከላከል ቅድመ ዝግጅት በየዓመቱ በኮሚሽኑ በማስገምገም የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለባቸው፤

ረ/ ሰራተኞች የእሳት ቃጠሎ አደጋን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል ስልጠና ከኮሚሽኑ ማግኘት አለባቸው፤

ሰ/ በእያንዳንዱ የሥራ ክፍሎች በቂና ተገቢ የሆኑ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች መደራጀት አለባቸው፤

ሸ/ በቴክኒክ ክፍሉ የሚዘረጋ ኤሌክትሪካል ኢንስታሌሽን ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች መዘጋጀትና ለሥራ የሚውሉ ማናቸውም ግብአቶች ደረጃቸውን የጠበቁ መደረግ ያለበትና ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ብቻ ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረግ አለበት፤

2) የቴሌ ኮሙኒኬሽን ተቋም ቴክኒካል ክፍል፡-

ሀ/ ማዞሪያ፣ ባትሪ ክፍል፣ ጀነሬተር፣ ሜን ሰርቨር ያለበት፣ ሜን ሰዊች፣ ማይክሮ ዌቭ ክፍሎች ውስጥ ዲቴክተር መገጠም አለበት፤

ለ/ አውቶማቲክ ሆኖ የሚሰራ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ እንደየ ሥራ ባህሪያቸው መሟላት አለበት፤

3) የሬድዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ኢንጅነሪንግ ዲፓርትመንት፣ መሳሪያ ጥገናና ክትትል፣ ፕሮዳክሽን፣ ስቱድዮ፣ የምስልና ድምጽ ላይብረሪ፣ ማሰራጫ፣ ጀነሬተር ክፍል በተለየ ሁኔታ እሳት የመቋቋም አቅም እንዲኖራቸው ማድረግና እና አውቶማቲክ የሆነ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ መገጠም አለበት፤

4) በተንቀሳቃሽ የሥርጭት ተሽከርካሪዎች ላይ ቢያንስ አንድ ባለ 5ኪ.ግ ሲ.ኦቱ ጋስ ለመሳሪያዎቹ፣ አንድ ባለ 6 ኪ.ግ ድራይ ፓውደር ለተሽከርካሪው መገጠም ይኖርበታል፤

5) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

6) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለአንድ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

7) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

8) የቴሌ ኮሙኒኬሽን ተቋም ቴክኒካል ክፍል ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

9) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

10)በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

11)የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

12)የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

13) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

14) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

15) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

16) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

17) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

18) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

19) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

20) እንደ የተቋሙ ምርትና አገልግሎት ባህሪና የተቀጣጣይነት ደረጃ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ እስከ 150 ሺ ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

21) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፤ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

22) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

23)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

24) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

25) ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ሆኖ የቢሮ ህንፃ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

26) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ሆኖ የቢሮ ህንፃ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

27)በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

28) የቴሌ ኮሙኒኬሽን ተቋም ቴክኒካል ክፍል ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

29) የቴሌ ኮሙኒኬሽን ተቋም ቴክኒካል ክፍል የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

30) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

31) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

32)የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

33) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

34) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

35)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 22. የትምህርት ተቋም የደህንነት መስፈርት

1) እያንዳንዱ የትምህርት ተቋም የመማሪያ ክፍል ከሃምሳ ሰዎች በላይ የመያዝ አቅም ያለው ወይም ከዘጠና ካ.ሜ. በላይ ስፋት ያለው ከሆነ ቢያንስ ሁለት የመውጫ በር ሊገጠምለት እና አንዱ ከአንዱ ተራርቀው መሰራት አለበት፤

2) የትምህርት ተቋሙ ህንጻ ወደ መውጫ ደረጃ የሚወስዱ ኮሪደሮች አውቶማቲክ የሆነ የእሳት ቃጠሎ አደጋ መቆጣጠሪያ የሚሆን መሳሪያ ካልተገጠመለት ከ46 ሜትር በላይ መሆን የሌለበት ሲሆን መሳሪያው ከተገጠመለት እስከ 61 ሜትር ርቀት ሊይዝ ይችላል፤

3) የትምህርት ተቋማት የመማሪያ ክፍል መውጫ ኮሪደር ግድግዳ ላይ ለተለያየ አገልግሎት የሚገጠሙ መሳሪያዎች አገጣጠም የመተላለፊያ ኮሪደሩን ስፋት መጠን በምንም አይነት ሁኔታ የሚያጣብቡ መሆን የለበትም፤

4) ከእያንዳንዱ የፎቅ ወለል በተቃራኒ አቅጣጫ ቢያንስ ሁለት የተለያዩ መውጫዎች እንዲኖሩት ተደርጎ ከየትኛውም ወለል በቀጥታ መሬት ላይ በሚገኘው ወለል በኩል ከህንጻው ውጪ እንዲያደርሱ ተደርገው መዘጋጀት አለባቸው፤

5) የትምህርት ተቋሙ መሰብሰቢያ አዳራሽ ከ50 በላይ ሰው የሚይዙ ከሆነ የመውጫ በር ወደ ሁለት አቅጣጫ ተከፋች ሆነው መዘጋጀትና ዘወትር ክፍት መደረግ አለባቸው፤

6) በትምህርት ተቋማ መኘታ፣ ምግብ ማዘጋጃ፣ ላይብረሪ፣ ኢንተርኔት ካፌ፣ ቤተ-ሙከራ፣ ኮምፒውተር ሰርቪስ፣ ጀነሬተር፣ ወርክ-ሾ ፕእና የልብስ ንጽህና መስጫ ክፍል ውስጥ አደጋን በጅምር ደረጃ ላይ እንዳለ አውቶማቲክ በሆነ መልኩ ሊጠቁሙ የሚችሉ መሳሪያዎች መገጠም ይኖርበታል፤

7) በትምህርት ተቋሙ ሌሎች ከእሳት ጋር ግንኙነት ያለው ሥራ የሚከናወንባቸው ክፍሎች ውስጥ የሚገኘው የህንጻው ግንባታ እሳትን ከአንድ ሰዓት በላይ ሊቋቋም እንዲችል ተደርጎ መገንባትአለበት፤

8) ህንፃዉ እሳትን ለአንድ ሰዓት ሊቋቋሙ ከሚችሉ የህንጻ ግብዓቶች እንደ ብሎኬት፣ ድንጋይ፣ ሸክላ ወይም ኮንክሪትና ተመሳሳይ ከሆኑ ነገሮች መገንባት አለበት፤

9) በህንፃው በየወለሉ የሚገኝ ባልኮኒ መዝግያ በር እና መስታዎት እሳትን ለግማሽ ሰዓት የሚቋቋም መሆን አለበት፤

10) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

11) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

12) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

13)በህንፃ ላይ የሚገጠመው መወጣጫ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በኮንክሪት የተገነባና የህንጻው ከፍታ ከ9 ሜትር በላይ ሲሆን ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ ደረጃ መኖር አለበት፤

14) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

15) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

16) የህንጻው የአደጋ ጊዜ መውጫ ደረጃ በኩል የሚገጠም በር እሳትና ሙቀት ለ30 ደቂቃ ያህል መቋቋም የሚችል፣ጭስ የማያሳልፍ እና በራሱ ጊዜ የሚዘጋ መሆን አለበት፤

17) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

18) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረገ ይገባል፤

19) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

20) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

21) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

22) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

23) የትምህርት ተቋም ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

24) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

25)የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

26)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

27)ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

28)ህንፃው ምድብ ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን ብርሃን የሚሰጥ መሳሪያ ከደህንነት ምልክት ጋር በእያንዳንዱ ወለል ላይ ሊገጠምለት ይገባል፤

29)ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

30)በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳተኞችና እርዳታ የሚሹ ተገልጋዮች መጠቀሚያ የሚሆን ኢቫክ ቸር ማዘጋጀትና ለመጠቀሚያ ከመደበኛ ደረጃ ውጭ በተዳፋት መልክ ሊዘጋጅ ይገባል፤

31) የትምህርት ተቋም ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

32) የትምህርት ተቋም የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

33)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

34)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

35) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

36) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

37) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

38)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 23. ማንኛዉም የህንጻ ግንባታ ዲዛይን፣ ሂደትና አጠቃቀም የደህንነት መስፈርት

1) ማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ በሚገኝበት ምድብ መሰረት የሚያስፈልገውን የአደጋ ስጋት ደህንነት መስፈርትን በዲዛይን ማካተት አለበት፤

2) ማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ ሰውን፣ ንብረትን እና ሌሎች ግንባታዎችን ለአደጋ በሚያጋልጥ ሁኔታ ዲዛይን መደረግና መገንባት የለበትም፤

3) ለማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ በስትራክቸራል ዲዛይን ውስጥ መሟላት ያለባቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የእሣትና የሌሎች አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መስፈርቶች መካተት አለበት፤

4) መሰረተ ልማት፣ ህንፃ ወይም የኢንዱስትሪ መዋቅር ይዘት፣ ስፋት፣ ከፍታ፣ ለተጠቃሚዎቹ ምቹና አስተማማኝ የሆነ፣ የተገልጋዩን ሁኔታና ብዛት፣ የአገልግሎት ዓይነት እና የአደጋ ተጋላጭነት ከግምት ውስጥ ያስገባ ዲዛይን መዘጋጀት አለበት፤

5) ለማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ ወይም መሰረተ ልማት የግንባታ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት በስትራክቸራል ዲዛይን ውስጥ መሟላት ያለባቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን እንደ እሣት፣ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ አውሎንፋስ፣ የመስመጥ፣ መደርመስ እና የሌሎች አደጋ መከላከያና መቋቋሚያ መስፈርቶች መካተታቸውን እና የህንጻ ስታንዳርድመጠበቁን በማረጋገጥ የግንባታ ፈቃድ መሰጠት አለበት፤

6) በህንጻ ውስጥ ነዋሪዎች ወይም ተጠቃሚዎች እያሉ የጥገና ሥራ የሚከናወን ከሆነ ለጥገና ሥራ የሚውል ማንኛውም ቁሳ ቁስና መሳሪያ ስራ ላይ ሲውል አሠሪው አካል እና ተጠቃሚዎቹ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

7) ማንኛውም አዲስ የተገነባ ህንጻ ወይም ግንባታ ወይም መሰረተ ልማት እንደ ምድቡ የአደጋ ደህንነት መሰፈርት ሳያሟላና የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋጋጫ ሳይሰጠው ህንጻውን ጥቅም ላይ ማዋል የለበትም፤

8) ማንኛውም ነባር ህንጻ ወይም ግንባታ ጥገና ወይም የተወሰነ ለውጥ በሚደረግባቸው ጊዜ ቀደም ሲል በህንፃው መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ማንኛውንም አደጋን ለመከላከል ብሎም ለመቆጣጠር የተገጠሙ ሲስተሞች ከዕድሳት ወይም ከጥገና በኋላ ስለመሟላታቸው ወይም ስለመተካታቸው ወይም ስለመስተካከላቸው ፍተሻ ተካሂዶና ተረጋግጦ ለህንጻው የአደጋ ደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የመውሰድ ግዴታ አለበት፤

9) የአደጋ ደህንነት መስፈረቶችን ያላሟላ ነባር ህንፃ ባለቤት የሆነ ሰው መስፈርቶችን ለማሟላት የሚጠበቅበትን የማድረግ ግዴታ አለበት፤

10) ማንኛውም የህንፃ ባለቤት የውሃ መቅጃ ሀይድራንት የግንባታው አካል ከግቢ ውስጥ ማስተከል አለባቸው፤ የሚተከለው ሀይድራንት ከአደጋ ምላሽ ሰጪ ተቋም ስታንዳርድ ጋር መጣጣም አለበት፤

11) ማንኛውም የጅምር ህንጻ ተጠቃሚ ከሚመለከተው አካል የመጠቀሚያ ፍቃድ መያዝ ኖርበታል፡፡

12) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

13) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

14) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

15) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

16) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

17) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

18) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 24. ለመኪና ማቆሚያ መዋቅሮች የደህንነት መስፈርት

ዝግም ሆነ ክፍት ከመሬት በላይም ሆነ በታች የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻ መዋቅሮች ወይም ለዚህ አገልግሎት የተገነባ ስትራክቸር የደህንነት መስፈርት

1) የጥገና ሥራ የሚከናወን ከሆነ የተሽከርካሪ ማቆሚያና የጥገና ክፍሉ መካከል ያለ የህንጻ አካል እሳትን ከአንድ ሰዓት በላይ መቋቋም እንዲችሉ በዲዛይኑ ላይ በግልጽ መቀመጥ አለበት፤

2) የትኛውም ወለል ቢያንስ ለተሽከርካሪዎች መግቢያና መውጫ ተለያይተዉ እንዲሁም በውስጡ ለሚኖሩ ሰዎች በተመሳሳይ ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

3) በቂ የአየር ምልልስ እንዲኖር የሚያስችል ሲስተም መዘርጋት ይኖርበታል፤

4) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

5) የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻ መዋቅሮች አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

6) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

7) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

8) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

9) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

10)በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

11)አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

12) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

13) በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

14) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

15) የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻ መዋቅሮች ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ኪ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር መኖር

ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

16) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

17) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

18) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

19) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

20) የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻ መዋቅሮች ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

21) የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጡ ህንጻ መዋቅሮች የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

22) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

23)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

24) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

25) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

26) የተገለጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ  የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

27) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 25. የአውሮፕላን ማቆሚያ ሃንጋር የደህንነት መስፈርት

1) የአውሮፕላን እድሳት በሚደረግበት ሥፍራ ወይም ሃንጋር ውስጥ ለአውሮፕላን መግቢያነት የሚያገለግለው አቅጣጫ ከ40 ሜትር ርቀት በማይበልጥና ቢያንስ ሁለት ቦታ ላይ የአውሮፕላን የእድሳት ወይም ጥገና ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ መዘጋጀት፤

2) የህንጻው የውስጠኛው የስትራክቸር አካል እሳትን በልዩ ሁኔታ የመቋቋም አቅም እንዲኖረው እና ለሰዎች መውጫነት የሚዘጋጀው ኮሪደር የሚኖረው የጉዞ ርቀት 30 ሜትር ተደርጎ መገንባት አለበት፤

3) ሊከሰት የሚችለውን የቃጠሎ አደጋ መቆጣጠሪያ የሚሆን የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ በሃንጋሩ ላይ አውቶማቲክ ሆኖ የሚሰራ ዲዛይን ተደርጎ መገጠም ይኖርበታል፤

4) ከፍተኛ አደጋ ስጋት ባለባቸው አካባቢዎች በቂና ተገቢ የእሳት ቃጠሎ አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ መመደብ ይኖርበታል፤

5) አዉሮፕላን ማረፊያና መነሻ ቦታ ቢያንስ 1 ስታንድባይ ፋየር ትራክ ከበቂ ባለ ሙያዎች ጋር መዘጋጀት አለበት፡፡

6) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

7) የአውሮፕላን ማቆሚያ ሃንጋር ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

8) በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

9) የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

10) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

11)በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

12)በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

13)አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

14)በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

15)በህንፃ ውስጥ የሚኖሩ አገልግሎት ሰጭዎችና ታሳቢ የተደረጉ ተገልጋዮችን ብዛት መሰረት ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ በቂ ስፍራ እንደአስፈላጊነቱ ከህንፃ ውስጥ ወይምውጭ መዘጋጀት አለበት፤

16)በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

17) የአውሮፕላን ማቆሚያ ሃንጋር ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ እስከ 150 ሺ ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፕሊንግ መገጠም አለበት፤

18) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

19) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

20) ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

21) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

22) የአውሮፕላን ማቆሚያ ሃንጋር ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

23) የአውሮፕላን ማቆሚያ ሃንጋር የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

24)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

25) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

26) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

27) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

28)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 26. የተሽከርካሪ ጥገና፣ ቀለም ቅብ እና ብረታ ብረት ስራ የደህንነት መስፈርት

1) የማከመቻና የጥገና ጋራዥ ግንባታ እሳትን ከ2 ሰዓት ላላነሰ ጊዜ እንዲቋቋሙ ካልተደረጉ በስተቀር ከሌሎች ህንጻዎች ጋር ተያይዘው መገንባት የለባቸውም፤

2) የሽያጭ፣ የማሳያ፣ ለቢሮና ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፣የመጠገኛ ክፍል ግድግዳ፣ወለል እና ኮርኒስ ግንባታ እሳትን ከ2 ሰዓት ላላነሰ ጊዜ የመቋቋም አቅም እንዲኖራቸው መደረግ አለበት፤

3) ከጥገና ማዕከል ወይም ጋራዥ ጋር ተያይዘው በሚገኙ ህንጻዎች ላይ የሚገጠሙ ኮርኒሶች ከጥገና ማዕከሉ ወይም ከተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራ የሚመጣን ጭስ በማያሳልፍ አይነት መዘጋጀት አለበት፤

4) የተሽከርካሪ ጥገና እና እድሳት የሚሰጡ ማዕከላት የወለሉ አሰራር በቀላሉ በእሳት ጉዳት ሊደርስበትና ፈሳሽ በማይመጥ ወይም በማይሰበስብ ግብዓት ሊገነባ ይገባል፤

5) የተሽከርካሪ እድሳት ሲካሄድ የሚወገድ ተቀጣጣይ ፈሳሽ ደረጃውን በጠበቀ ግንባታ በተዘጋጀለት ስፍራ ማጠራቀምና በአካባቢው ብክለት ወይም ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ ስራ ላይ መዋል ወይንም መወገድ ይኖርበታል፤

6) የሞተር ጥገና በሚካሄድበት ወርክሾፕ ውስጥ ከጥገና ሥራ በኃላ ሞተር የሚፈተሽ ከሆነ ይህ ከመከናወኑ በፊት በሞተሩ የጭስ ማስወገጃ መስመር ላይ የሚገጠምና ከጥገና ወርክሾፑ ጣራ አናት በኩል የተዘጋጀ የጭስ አወጋገድ ሲስተም ሊኖረው ይገባል፤

7) የጥገና ማዕከሉ የግድግዳ ከፍታ በአካባቢው በቂ የሆነ የአየር ምልልስ እንዲኖር እንዲያስችል ቢያንስ ከ4 ሜትር ማነስ የለበትም፤

8) ብየዳና ቅጥቀጣ ሥራ የሚከናወንበት ክፍል ውስጥ በቅርብ ርቀት ምንም አይነት የሚቀጣጠል ነገር ፈሳሽም ሆነ ጠጣር ነገሮች መኖር የለባቸውም፤

9) ብየዳ የሚከናወንባቸው የጋስ መያዣ ሲሊደር ደህንነትና አደጋ የማያስከትል መሆኑን ዘወትር ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤

10)የጋስ ብየዳ ሥራ ከሚከናወንባቸው የአሰራር ሂደት አንዱ ካልሲያም ካርቦይድን ከውሃ ጋርበማደባለቅ አሲቲሊን በማምረትና ወዲያውኑ ብየዳ የሚከናወንባቸው ሲሊንደር በሞዲፊኬሽን ስራ የሚመረቱ በመሆኑ ይህን ለብየዳ ሥራ ክንውን የሚያገለግልን መሳሪያን ጉዳዩ በሚመለከተው አካል የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ ካልሆኑ በስተቀር ለዚህ ሥራ ማከናወኛ መዋል አይኖርባቸውም፤

11)አርክ ዌልዲንጉ የሚሰራበት መሳሪያ ጉልበት እንዲያገኝ የሚደረግበት የኃይል ምንጭ እና ኤሌክትሪክ ካረንት ተሸካሚው ገመድ ወይም ኬብል ከመመጣጠን በተጨማሪ ምንም አይነት የተቀጣጠለ የኤሌክትሪክ ገመድ መጠቀም አይገባም፤

12)አርክ ዌልዲንግ መከናወን ያለበት በዘርፉ በቂ እውቀት ባለው ባለሙያ መሆን ይኖርበታል፤

13)የቀለም ቅብ ሥራ በተከለለ ክፍል ውስጥ መከናወን ያለበት ሆኖ ይህ ሥራ በሚከናወንበት ወርክሾፕ በ6 ሜትር ርቀት ክልል ውስጥ ክፍት እሳት ወይም ብልጭታ ሊያመነጭ የሚችል መሳሪያ መጠቀም የተከለከለ ነው፤

14)ማንኛውም አይነት የቀለም ቅብ ሥራ የተከናወነበት ተሽከርካሪ ቅቡ ሳይደርቅ የተሽከርካሪ ሞተር ማስነሳት ፈጽሞ የተከለከለ ነዉ፤

15)በተሽከርካሪ በተወሰነ አካል ላይ ብቻ ለሚደረግ የቀለም ቅብ ሥራ ከመቀቢያ ወርክሾፑ ውጭ ሆኖ በአካባቢው ከ6 ሜትር ባነሰ ርቀት ክልል እሳት ወለድ መሳሪያ የማይጠቀሙ ከሆነ ይህን ማከናወን ይቻላል፤

16)በጥገና ማዕከሉ ውስጥ ማንኛውንም አይነት የሥራ ሂደት አደጋን እንዳያስከትል የሚከታተል የሴፍቲ ኦፊሰር/ተጠሪ እንዲኖር መደረግ አለበት፤

17)የሰራተኞች የልብስ መቀየሪያ ክፍል እራሱን የቻለና የተዝረከረከ አሰራር ማስወገድ እንዲቻል ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ልብስ ማስቀማጫ የብረት ካቢኔት ወይም ቁም ሳጥን ሊኖረው ይገባል፤

18)በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትሪክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

19)የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

20)በህንፃ ላይ ማንኛውንም አይነት ግንባታና የማስተካከል ሥራ ከመሰራቱ በፊት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤

21)የኮሪደሩን ርዝመት ከግምት ያስገባ እስከ 30 ሜትር ፋየር ሆስ በህንጻ ላይ መገጠም አለበት፤

22) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

23) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

24)በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

25)አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

26) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

27) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

28) የተሽከርካሪ ጥገና፣ ቀለም ቅብ እና ብረታ ብረት ስራ ግቢዉ ዉስጥ ፋየር ሃይድራንት በ40,000 ስኩዌር ካ.ሜ ክልል ውስጥ የሚተከል ከ115ሺ. እስከ 150 ሺ. ውሀ ክምችት ጋር መኖር ያለበት ሆኖ የመገጣጠሚያዎች መጠን 2½ ኢንች የሆነ ኢኒስታንታኒየስ ካፐሊንግ መገጠም አለበት፤

29) ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

30) የኮሚሽኑንና የሌሎችንም ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች እና አምቡላንሶች መተላለፊያና መቆሚያ ሥፍራ ቀድሞ ማዘጋጀትና መተላለፊያ መንገዶች ከማንኛውም ፈጣን የአደጋ ምላሽ ከመስጠት ከሚያውኩ ነገሮች ነጻ ማድረግ ይገባል፤

31)ህንፃው ከህንፃ ምድብ ሁለትና በላይ ከሆነ፡-

ሀ/ አማራጭ የሃይል መስጫ አዉቶማቲክ ጀነሬተር ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

ለ/ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ ሳይቋረጥ የአደጋ ጊዜ ብርሀን የሚሰጥ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

32) ህንፃው ምድብ ሦስትና ከዛ በላይ ህንፃ ከሆነ በኤሌክትሪክና በነዳጅ የሚሰራ ፋዬር ፓምፕ ፣ አደጋ መከሰቱን የሚጠቁም ዲቴክተር፣ የማንቂያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ መውጫ አቅጣጫን የሚያመለክት ንድፍ ሊኖረው ይገባል፤

33) የተሽከርካሪ ጥገና፣ ቀለም ቅብ እና ብረታ ብረት ስራ ግቢዉ ዉስጥ ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

34)የተሽከርካሪ ጥገና፣ ቀለም ቅብ እና ብረታ ብረት ስራ ግቢዉ ዉስጥ የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

35) የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

36) ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

37) የአደጋ ጊዜ የአሰራር መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለነዋሪዎች ፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ እንዲያዉቁት ማድረግ እና በቂ የልምምድ ጊዜ በማዘጋጀት ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዉን በባለቤትነት መንፈስ እንዲሰሩ ማድረግ ያገባል፤

38) በህንጻ ላይ የመብረቅ መከላከያ መገጠም አለበት፤

39) የተገልጋይና የህንፃውን ስፋት ታሳቢ ያደረገ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ መዘጋጀት አለበት

40)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 27. የእሳት አደጋ ማሳወቂያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችና መገልገያዎች ከዉጪ ሀገር ማስገባት፣ መሙላት፣ ማከፋፈል እና መጠገን ሥራ የሚያከናዉኑ ተቋማት የደህንነት መስፈርት

1) ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ የእሳት ማጥፊያና ማሳወቂያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ መስፈርትና የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ያገኙ ስለመሆናቸው ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል፤

2) እያንዳንዱ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ ሲሊደር ከአምራች ድርጅቱ ምን ያህል የታመቀ የጋስ ግፊት ወይም ባር መሸከም እንደሚችል የሚገልጽ መግለጫ ሊኖረው ይገባል፤

3) እያንዳንዱ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ ላይ በውስጡ ስለያዘው የኬሚካል አይነት፣ አያያዝና አጠቃቀም በእንግሊዘኛ የተጻፈ መግለጫ ሊኖረው ይገባል፤

4) ከፋብሪካው ተመርቶ ሲመጣ እንዲይዝ ከተደረገው የእሳት ማጥፊያ ኮምፓውንድ ውጭ የጥገና ወይም የመሙላት ሥራ ማከናወን ፈጽሞ የተከለከለ ነው፤

5) ማንኛውም በዓለም አቀፍ ደረጃ መስፈርት ከደረጃ ውጭ የተደረጉ፣ የተከለከሉ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያን ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት፣ በጥቅም ላይ ማዋል እና መሙላት የተከለከለ ነው፤

6) ለእሳት ማጥፊያ የሚያገለግሉ ኬሚካሎችን የመያዣ ሲሊደሮችን አስመስሎ ማምረት ወይም ሲሊደሩን በይዶ ጥቅም ላይ ማዋል ፣ብይድ ያለበት መሆኑን እያወቁ መሙላት የተከለከለ ነው፤

7) የእሳት አደጋ መከላከያ በጅምር ደረጃ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን የሚሞሉ ፤የሚፈትሹና የሚያረጋግጡ ተቋማት ተሸከርካሪን ጨምሮ አስፈላጊውን የስራ መሳሪያ በወርክሾፕቻቸው አማልተው መገኘት አለባቸው፡፡

8) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

9) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

10)በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

11)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

12)እያንዳንዱ ድርጅት የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

13)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

14)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

15) የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 28. ተለይቶ መስፈርት ያልተዘጋጀላቸዉ አነስተኛና የተለያዩ የመንግስትና የግል ስራዎችን የሚሰሩ ልዩ ልዩ ተቋማት የደህንነት መስፈርት

1) ለእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ ብቻ ተብሎ የተዘጋጀ በቂ የውሃ ክምችት ሊኖረው ይገባል፤

2) በህንጻ ውስጥ የሚዘረጋ ኤሌክትክ ደረጃውን የጠበቀ ፤ ተገቢ እውቅና ባለው ተቋምና ባለሙያ መከናወን አለበት፤

3) የተለያየ አገለግልግሎት የሚሰጥ ህንጻ አደጋን ለመከላከል የጋራ ወይም የግል ኃላፊነት መውሰድ የሚችል ባለሙያ ወይም ኮሚቴ ሊኖር ይገባል፤

4) የህንጻው ከፍታ ከሶስት ወለል በላይ ከሆነ አንድ ተጨማሪ በአደጋ ጊዜ መጠቀሚያ የሚሆን መወጣጫ ደረጃ ከእያንድንዱ ወለል ጋር ተገናኝቶ በቀጥታ መሬት የሚያደርስና ወደ አደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ቦታ ለመሄድ የሚመች ሊኖረው ይገባል፤

5) በእጅ የሚያዙ ጅምር እሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በህንጻው ውስጥ በተገቢ ርቀትና አስፈላጊነት በማደራጀት ለአደጋ ስራ ዝግጁነታቸው በየ6 ወሩ በኮሚሽኑ እውቅና ባለው አካል መረጋገጥ አለበት፤

6) በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሙያ የሰለጠነ ወይም ሰርተፍኬት ያለው የሰዉ ኃይል እንደ አስፈላጊነቱ እንዲኖር ማድረገ ይገባል፤

7) አደጋን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችሉ፣ የሚከለክሉ፣ የሚያስገድዱ፣ የሚያስጠነቅቁ እና መረጃ የሚሰጡ ምልክቶችን በተቋም እና ህንጻ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ስፍራዎች ላይ መሟላት አለበት፤

8) በድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለተጎጂዎች የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ለመስጠት የሚያስችል የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና መስጫ መሳሪያ ማሟላት አለበት፣

9) በጋሪ (ዊልቸር) ለሚንቀሳቀሱ ተጠቃሚዎች ተዳፋት (Ramp) መገጠም አለበት፤

10)ከእሳት ጋር የተገናኘ ከቆሻሻ ማቃጠል ፣ሲጃራ ማጨስ ፤ ለተለያየ አገልግሎት ግልፅ እሳት ሲቀጣጠል በዙሪያው ካለ ተቀጣጣይ ቁስ ቢያንስ 10 ሜትር ርቀት ባላነሰ የራቀና የተቀጣጣይ ቁስን ባህሪ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

11)የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት እንደ የአስፈላጊነቱ በስራ ቦታ አሟልቶ መጠቀም ይገባል፤

12)በእያንዳንዱ ድርጅት ውስጥ እንደየስራ ባህሪውና አስፈላጊነቱ የቆሻሻና የብናኝ ማከማቻ ወይም መሰብሰቢያ ሲስተም ማዘጋጀት ይኖርበታል፤

13)እያንዳንዱ ድርጅት የደህንነት መስፈርት ማሟላትና የኮሚሽኑን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲሁም በየአመቱ ማሳደስ አለበት፤

14)የአደጋ ጊዜ ዕርዳታ ሰጪ ተቋማትን የስልክ ቁጥሮች በማዘጋጀት በግልጽ ስፍራ መ ለ ጠ ፍ ይኖርበታል፤

15)ስለ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ለነዋሪዎች፣ ሰራተኞቹና ለተቋሙ ማህበረሰብ የግንዛቤ ስልጠና መስጠትና እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፤

16)የእቃዎች አደራደርና አቀማመጥ ተቀጣጣይ የሆኑና ያልሆኑ ተለይቶ በአግባቡ በመለየት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## በእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት የሚሰጥ የደረጃ መስፈርት

### 29. የእሳት ማጥፊያ ና ማሳወቂያ መሳሪያዎች ስራላይ ለተሰማሩ ለሁሉም ደረጃ ምዝገባ ምስክር ወረቀት መስፈርት

የእሳት ማጥፊያና ማሳወቂያ መሳሪያዎችን እና የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳትን የሚያስመጣ፣ የሚያከፋፍል፣ የሚሞላና የሚጠግን ተቋም፡-

1) ስራዉን ለማከናወን የሚያስችል በቂ ቢሮ ማዘጋጀት አለበት፤

2) ለስራ የሚገለገልበት ተሽከርካሪ ሊኖረዉ ይገባል፤

3) የቴክኒክና ሽያጭ ሰራተኞች ቢያንስ የእሳት ቃጠሎ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስልጠና ከኮሚሽኑ እንዲወስዱ ማድረግ አለበት፤

4) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ማንኛውም የደህንነት መሳሪያ የዓለም አቀፍ ስታንዳርድ መስፈርትና የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ያገኙ ስለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

5) እያንዳንዱ የእሳት መቆጣጠሪያ ሲሊንደር ከአምራች ድርጅቱ ምን ያህል የታመቀ የጋዝ ግፊት ወይም ባር መሸከም እንደሚችል የሚገልጽ መግለጫ እናተለጣፊ ያልሆነ ዓለም ዓቀፍ ቀለም (permanent international color code) በእያንዳንዱ ሲሊንደር ላይ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፤

6) የተለያዩ መጠንና አይነት ያላቸው የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ በቂ ክምችት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፤

7) የሚጠቀምባቸዉ ማሽኖች የተቋሙ ባለቤትነት የሚገልጽ በማሽኖች ላይ በማይለቅ ጽሁፍ ተጽፎ ወይም የደረሰኝ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

### 30. ደረጃ አንድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት መስፈርት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

የእሳት መከላከያ፣ መቆጣጠሪያ፣ ማሳወቂያ መሳሪያዎችን እና የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት የሚያስመጣ፣ የሚሸጥ፣ የሚያከፋፍል፣ የሚሞላና የሚጠግን ተቋም ደረጃ አንድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ፡-

1) ወርክሾፕ (የሲሙሌሽንና ማሳያ መሳሪያዎች ያካተተ) ፤

2) የተለያየ ደረጃ የሚገኙ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ መጠን መለኪያ ከ1-50ና ከዚያ በላይ ኪ.ግ መመዘን የሚችል ዲጅታል ሚዛን፤

3) ናይትሮጅን መሙያ ፣ ካርቦንዳይ ኦክሳይድ መሙያ እና ድራይ ፓዉደር መሙያ ማሽን፤

4) የሲሊንደሮችን ጥንካሬ ለመለካት የሚያስችል ሀይድሮ ስታቲክ ፕሬዥር ቴስት ማድረጊያ መሳሪያ እና

5) ብረትና እንጨት መብሻ (ድሪለር) ፣ ቫይስ፣ ለጥገና ሥራ የሚያስፈልግ የተለያዩ አይነት መሳሪያዎች ማሟላት አለበት፤

## 31. ደረጃ ሁለት ምዝገባ ምስክር ወረቀት መስፈርት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የእሳት መከላከያ፣ መቆጣጠሪያ፣ ማሳወቂያ መሳሪያዎችን እና የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት የሚያስመጣ፣ የሚሸጥ፣ የሚያከፋፍል፣ የሚሞላና የሚጠግን ተቋም ደረጃ ሁለት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ ብረትና እንጨት መብሻ (ድሪለር) ፣ ቫይስ፣ ለጥገና ሥራ የሚያስፈልግ የተለያዩ አይነት መሳሪያዎች ማሟላት አለበት።

## 32. ደረጃ ሶስት ምዝገባ ምስክር ወረቀት መስፈርት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

የእሳት መከላከያ፣ መቆጣጠሪያ፣ ማሳወቂያ መሳሪያዎችን እና የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት የሚያስመጣ፣ የሚሸጥ፣ የሚያከፋፍል፣ የሚሞላና የሚጠግን ተቋም ደረጃ ሦስት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ፡-

1) ወርክሾፕ (የሲሙሌሽንና ማሳያ መሳሪያዎች ያካተተ) ፤

2) የተለያየ ደረጃ የሚገኙ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ መጠን መለኪያ ከ1-50ና ከዚያ በላይ ኪ.ግ መመዘን የሚችል ዲጅታል ሚዛን፤

3) ናይትሮጅን መሙያ ፣ ካርቦንዳይ ኦክሳይድ መሙያ እና ድራይ ፓዉደር መሙያ ማሽን፤

4) የሲሊንደሮችን ጥንካሬ ለመለካት የሚያስችል ሀይድሮ ስታቲክ ፕሬዥር ቴስት ማድረጊያ መሳሪያ እና

5) ብረትና እንጨት መብሻ (ድሪለር) ፣ ቫይስ፣ ለጥገና ሥራ የሚያስፈልግ የተለያዩ አይነት መሳሪያዎች ማሟላት አለበት፤

## 33. ደረጃ አራት ምዝገባ ምስክር ወረቀት መስፈርት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የእሳት መከላከያ፣ መቆጣጠሪያ፣ ማሳወቂያ መሳሪያዎችን እና የግል ጉዳት መከላከያ አልባሳት የሚያስመጣ፣ የሚሸጥ፣ የሚያከፋፍል፣ የሚሞላና የሚጠግን ተቋም ደረጃ ሦስት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመውሰድ ብረት እና እንጨት መብሻ (ድሪለር)፣ ቫይስ፣ ለጥገና ሥራ የሚያስፈልግ የተለያዩ አይነት መሳሪያዎች ማሟላት አለበት፤

# ክፍል አራት

# ስለተከለከሉ ድርጊቶችና ግዴታዎች

## 34. የተከለከሉ ድርጊቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ድርጊቶች የተከለከሉ ናቸው፡-

1) በተለያዩ ስፍራዎች ላይ ለአደጋ መቆጣጠር ሥራ የሚውሉ ኮሚሽኑ በአደጋ ጊዜ የሚጠቀምባቸው ሃይድራንቶችን ለብልሽት መዳረግ፣ ከኮሚሽኑ ዕውቅና ውጪ ከቦታ ቦታ ማንቀሳቀስ፣ ወደግል ይዞታ ውስጥ ማስገባት በላያቸው ግንባታ ማካሄድ ሌሎች አካላት በዚህ መሳሪያ መጠቀም፤

2) ለድንገተኛ አደጋ መቆጣጠሪያነት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን እና የግል ጉዳት መከላከያ መሳሪያዎችን አስመስሎ ማምረት (ሞዲፊኬሽን) ሥራ መሥራት፤

3) የደህንነት መስፈርቶች ሳይሟሉ እንደተሟሉ አድርጎ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት ወይም መቀበል፤

## 35. ስለግዴታ

ማንኛውም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1) በየዓመቱ የሚታደሰውን የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማሳደስ፤

2) የተገጠሙ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያና ቅድመ አደጋ መከላከያ መሳሪዎች ወቅቱን የጠበቀ የባለሙያ ማረጋገጫ እንዲያገኙ ማድረግ፤

3) በማንኛውም ተሽከርካሪ ላይ ተገቢዉን የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ ማሟላት፤

4) በኮሚሽኑ በእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ የሰለጠነ በቂ ባለሙያ ማሟላት፤

5) በስብሰባ፣ በቲያትርና በሲኒማ ቤቶች ታዳሚዎች በተዘጋጀው ወንበር ልክ እንዲስተናገዱ የማድረግ፤

6) የድንገተኛ አደጋዎችን ህግና አሰራር እንዲተገበር ማድረግ፤

7) የኮሚሽኑ የቅድመ አደጋ መከላከል እና አደጋ መቆጣጠር ባለሙያዎች በስራ ላይ እንዳሉ ጣልቃ

አለመግባት እና የሚፈለግበትን የሙያ ግዴታ በአግባቡ እንዲወጣ ያለማወክ፤

8) ሀሰተኛ የአደጋ ጊዜ ጥሪ በስልክ ወይም በአካል በመምጣት ጥሪ ማከናወን፣ ለሌላ ተግባር የአደጋ ጊዜ መቀበያን ስልክ መስመር አለመያዝ ወይም አለማጨናነቅ፤

9) ከህግ አግባብና ከሚፈቀድ መጠን በላይ ለአደጋ ክስተት ምክንያት የሚሆኑ ተቀጣጣይ ፈንጂ ኬሚካልና ቁሳቁሶችን በራስ ይዞታ ግቢ ውስጥ ያለአግባብ አለማከማቸት፤

10) በኮሚሽኑና ኮሚሽኑ እውቅና በሰጣቸው አካላት የሚሰጥ የሙያ ምክርና ቴክኒክ ድጋፍ መሰረት ያደረገ በቂና ተገቢ የሆኑ የአደጋ መከላከያና መቆጠሪያ መሳሪያ የማሟላት፤

11) ህንጻ ለተገቢው ጥቅም ለተገልጋይ ክፍት ከመሆኑ በፊት በኮሚሽኑ ባለሙያዎች የአደጋ ደህንነት ፍተሻ የማስደረግና የብቃት ማረጋገጫ ከኮሚሽኑ ማግኘት፤

12) የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ መሳሪዎችን በአመት ሁለት ጊዜ በኪሚሽኑ እውቅና በተሰጣቸው ድርጅቶች አማካኝነት የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ የማድረግ፤

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 36. የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ባለሙያ ስለመመደብ

1) የመንግስት፣ የህዝብና የግል ተቋም እንደ ተቋሙ ስፋትና አገልግሎት አሰጣጥ መሰረት በመደበኛነት ወይም በያዙት ሥራ ላይ በተደራቢነት የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ባለሙያዎችን መመደብ አለበት፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በእያንዳንዱም ተቋም ዉስጥ የሚመደቡ ባለሙያዎች ብዛት፡-

ሀ/ ሃምሳና ከዚያ በታች የሆኑ ሰራተኞች ባሉበት 1 ባለሙያ

ለ/ ከ50-100 ሠራተኞች ባሉበት 3 ባለሙያ

ሐ/ ከ101-200 ሠራተኞች ባሉበት 4 ባለሙያ

መ/ ከ201-500 ሠራተኞች ባሉበት 6 ባለሙያ

ሰ/ ከ501-1000 ሠራተኞች ባሉበት 8 ባለሙያ

ረ/ ከ1000 ሠራተኞች በላይ ባሉበት 10 ባለሙያ ይሆናል፤

## 37. ክትትልና ቁጥጥር

በከተማው የሚገኙ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን፣ የእሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን እንዲያከፋፍሉ በህግ ውክልናና ፍቃድ የተሰጣቸው ተቋማትን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሲሆንም የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል

## 38. ብቃት ማረጋገጫ

ማንኛውም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፤ እንዲሁም የእሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ወይም በንብረቱ የሚጠቀመው አካል በሚደረግለት ፍተሻና የሚጠበቅበት የአገለግሎት ክፍያ በመፈፀም በየዓመቱ የሚታስ  የእሳት አደጋ ደህንነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መያዝ አለበት፡፡

## 39. የእርምጃ አወሳሰድና አስተዳደራዊ ቅጣት

1) ኮሚሽኑ በማንኛውም ተቋም ላይ በየጊዜው የአደጋ ስጋት ደህንነት ፍተሻዎችን በማካሄድ ለተጓደሉ መስፈርቶች በስድስት ወር ጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ የፅሑፍ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በወቅቱ ያላሳደሰ ከሆነ በዘገየበት ጊዜ ልክ በኮሚሽኑ የአገልግሎት ክፍያ መሰረት ተቀጥቶ እንዲያሳድስ ይደረጋል፤

3) በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ከሶስት ጊዜ በላይ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ ትዕዛዝ የሰጠ ወይም ከደንብና መመሪያዎች ተቃራኒ የሆኑ ተግባራትን የፈጸመ የመስሪያ ቤት ኃላፊ ወይም ባለሙያ ለሚደርሰው ጉዳት በግል ተጠያቂ ይሆናል፤

4) የሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ እና የቅጣት መቀጮ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ሰንጠረዥ አራት መሰረት ይፈፀማል፤

## 40. ቅሬታ ስለማቅረብ

1) አስተዳደራዊ ቅጣት የተዋሰደበት የኮሚሽኑ ሰራተኛ ቅጣቱ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በየደረጃው ለሚገኙ ኃላፊዎች ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ኮሚሽኑ ቅሬታ በደረሰው በ30 ቀናት ውሰጥ የቀረበውን ቅሬታ አጣርቶ ምላሽ መሰጠት አለበት፤

3) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ተቋም የእገዳ ወይም የስረዛ ቅጣት ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ኮሚሽኑ ቅሬታ በደረሰው በ30 ቀናት ውሰጥ የቀረበውን ቅሬታ አጣርቶ ምላሽ መሰጠት አለበት።

## 41. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒሰቴር ተመዝግቦ በኮሚሽኑ እና በፍትህ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሕዳር፣ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ፍቅሬ ግዛው

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ

ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር

# ልዩ ልዩ አባሪ ሰንጠረዥ

## አባሪ ሰንጠረዥ አንድ .የጋስ ማከማቻ ጋን ተከላ ከተለያዩ ተቋማትና ከባቢያዊ ነገሮች የሚኖረዉ ርቀት

| ተ.ቁ | የተለያዩ ተቋማትና እና ከባቢያዊ ነገሮች | ከ50 ቶን በላይ | ከ30-50 ቶን | ከ15-30 ቶን | ከ6-15 ቶን | ከ6ቶን በታች ሲሆን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | በአካባቢ ከሚገኝ ዛፎች | 20ሜትር | 10ሜትር | 10ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 2. | ከተከማቸ እንጨት | 20ሜትር | 10ሜትር | 10ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 3. | ከፍሳሽ ማስወገጃ መስመር | 20ሜትር | 5ሜትር | 10ሜትር | -- | 5ሜትር |
| 4. | ከጋስ መሙያ መስመር | 7.5ሜትር | 5ሜትር | 5ሜትር | -- | 3ሜትር |
| 5. | ከይዞታው አጥር | 30ሜትር | 15ሜትር | 7.5ሜትር | -- | 5ሜትር |
| 6. | ከክፍት እሳት | 20ሜትር | 15ሜትር | 10ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 7. | ከባቡር መስመር | 20ሜትር | 15ሜትር | 15ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 8. | ከሌሎች ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች | 20ሜትር | 15ሜትር | 10ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 9. | ከከፍተኛ የኤሌክትሪክ መስመር | 20ሜትር | 15ሜትር | 10ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 10. | የውሃ ምንጭ ከሆነ አካባቢ | 20ሜትር | 10ሜትር | 10ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 11. | ከመኖሪያ ህንጻ | 20ሜትር | 15ሜትር | 10ሜትር | 7.5ሜትር | 5ሜትር |
| 12. | ከህዝብ መተላለፊያ መንገድ | 30ሜትር | 15ሜትር | 10ሜትር | -- | 5ሜትር |
| 13. | ለሌሎች አገልግሎትከሚሰጥ ህንጻ | 75ሜትር | 10ሜትር | 25ሜትር | 15ሜትር | 7.5ሜትር |

## አባሪ ሰንጠረዥ ሁለት . በአነስተኛ ደረጃ የሚገኙ የቡታ ጋስ መያዥ ሲሊንደር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሊጠበቅ የሚገባው ርቀት፡-

| ተ.ቁ | ክፍሉቹ | ከ50 ኪግ | ከ51-250ኪ ኪግ | ከ250 ኪግ በላይ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ከመኖሪያ ህንጻ | 1 ሜትር | 2 ሜትር | 3 ሜትር |
| 2 | የተለያየ አገልግሉት ከሚሰጡ ህንጻዎች | 2 | 3 ሜትር | 3 ሜትር |
| 3 | ከፍሳሽ ማስወገጃና ከአየር ማናፈሻ መስመር፣ከምድር በታች ከሆነ ክፍል | 2 ሜትር | 3 ሜትር | 3 ሜትር |
| 4 | ክፍት ከሆነ እሳት ቡቴን ጋስ | 1 ሜትር | - | - |
| 5 | ክፍት ከሆነ እሳት ፕሮፔን ጋስ | 3ሜትር | 3 ሜትር | 5 ሜትር |
| 6 | ከይዞታ አጥር | 3 | 3 ሜትር | 3 ሜትር |
| 7 | ከህዝብ መተላለፊያ መንገድ | 3 | 3 ሜትር | 3 ሜትር |
| 7 | በኤሌክትሪ ኃይል ከሚሰሩ መሳሪያዎች ቡቴን ጋስ ሲሊደሮች | 2 ሜትር | - | -- |
| 8 | በኤሌክትሪ ኃይል ከሚሰሩ መሳሪያዎች ፕሮፔን ጋስ ሲሊደሮች | 3 ሜትር | - | -- |
| 9 | ከኤሌክትሪክ መስመር | 3 | 5 ሜትር | 7.5ሜትር |

## አባሪ ሰንጠረዥ ሶስት . ለቡታ ጋስ የእሳት ቃጠሎ አደጋ መቆጣጠር ሥራ የሚያስፈልጉ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች፡

| ተ.ቁ | የቡታ ጋስ የክምችት መጠን | የእሳት ቃጠሎ አደጋን ለመቆጣጠር የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች አነስተኛ መስፈርት |
|---|---|---|
| 1 | ከ5 ቶን በታች | 14 ኪ.ግ ፓውደር ፣ ስፕሪንኪለር ሲስተም |
| 2 | ከ5 እስከ 10 ቶን የማከማቻ ጋን | 24 ኪ.ግ ፓውደር፣ ስፕሪንኪለር ሲስተም |
| 3 | ከ11 እስከ ከ15 ቶን የማከማቻ ጋን | 26 ኪ.ግ ፓውደር እና ስፕሪንኪለር ሲስተም |
| 4 | ከ16 እስከ 30 ቶን የማከማቻ ጋን | 29 ኪ.ግ ፓውደር፣ ከ100-125ኪ.ግ ተንቀሳቃሽ ፓውደር፣ ስፕሪን ኪለር ሲስተም፣ አንድ ፋር ሃይድራንት |
| 5 | ከ30 እስከ 50 ቶን የማከማቻ ጋን | 29 ኪ.ግ ፓውደር፣ከ100-125ኪ.ግ ተንቀሳቃሽ ፓውደር፣ ስፕሪን ኪለር ሲስተም፣አንድ ፋየር ሃይድራንት |
| 6 | ከ50 ቶን በላይ የማከማቻ ጋን | 30 ኪ.ግ ፓውደር፣ ከ150-225ኪ.ግ ፓውደር፣ ስፕሪንኪለር ሲስተም፣ አንድ ፋየር ሃይድራንት |

## አባሪ ሰንጠረዥ አራት . የእርምጃ አወሳሰድና አስተዳደራዊ ቅጣት

| የጥፋት ደረጃ | የጥፋት አይነት | አስተዳደራዊ ቅጣት (የቅጣት መጠን) | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 3 | በቂና ተገቢ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን ያላሟላ፤<br><br>እንደ ተቋሙ ስፋትና የሚሰጠዉ አገልግሎት አይነት አላርም ያላሟላ፤<br><br>እንደአስፈላጊነቱ ዓለም አቀፍ የደህንነት ምልክቶችን ያላሟላ፣ የአደጋ ጊዜ መሰብሰቢያ ያላዘጋጀ፣ እንደ ተቋሙ አይነትና ስፋት በአደጋ ጊዜ ከህንጻዉ የመልቀቅ ንድፍ ያላዘጋጀ፣ የአደጋ ጊዜ ምላሽ አሰጣጥ እቅድ ያላዘጋጀ፣ የመገናኛ መሣሪያዎችንና የድንገተኛ አደጋ የጥሪ መቀበያ ስልኮችን ያላዘጋጀ፣ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በሚሰጡት የሙያምክርና ድጋፍ መሰረት የጋራ /የቅንጅት/የደህንነት ጥበቃ ልምምድ በአመት አንድ ጊዜ ያላደረገ እና የድርጅቱ ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስልጠና ያላሰለጠነ፡፡<br><br>የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን ያላሟላ፤<br><br>የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ያደረገ፣ ያልተባበረ፣ | ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ፣ በስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲያስተካክል ሙያዊ ምክር ግብረመልስ ይሰጠዋል፡፡<br><br>ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ በሶስት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲያስተካክል የጽሁፍ ማስጠንቀቅያ ይሰጠዋል፡፡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ካላስተካከለ 10000 ብር ከፍሎ ድጋሚ እንዲያስተካክል እድል ይሰጠዋል፡፡ 10000 ብር ከፍሎ ድጋሚ እንዲያስተካክል የተሰጠዉን እድል መጠቀም ካልቻለ የስራ ፍቃዱ እንዲታገድ ፈቃዱን ለሰጠው አካል የማሳወቅ ስራ ይሰራል፡፡ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | የድርጅቱ ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስልጠና ያላሰለጠነ፤<br><br>በቂና ተገቢ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን ያላሟላ፤<br><br>እንደ ተቋሙ ስፋትና የሚሰጠዉ አገልግሎት አይነት አላርም ያላሟላ፤ የደህንነት ባለሙያ ያልመደበ ማንኛዉም ተቋም የኮሚሽን መ/ቤቱን የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ የሌለዉና አመታዊ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን ያላሳደሰ፤<br>የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በሚሰጡት የሙያምክርና ድጋፍ መሰረት ፋየር ፓምፕ ያላሟላ፤<br>የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን ያላሟላ፤<br>የኤሌክትሪክ ገመዶችን በአግባቡ ያልዘረጋ፤<br>እንደ ተቋሙ ስፋት የአደጋ ጊዜ መብራት ያላሟላ፤<br>የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በሚሰጡት የሙያምክርና ድጋፍ መሰረት የደህንነት ጥበቃ ልምምድ በአመት አንድ ጊዜ ያላደረገ፤<br>የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ያደረገ፣ ያልተባበረ፣ | ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ፣ በስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲያስተካክል ሙያዊ ምክር ግብረመልስ ይሰጠዋል፡፡<br><br>ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ፣ በሶስት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲያስተካክል የጽሁፍ ማስጠንቀቅያ ይሰጠዋል፡፡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ካላስተካከለ 50000 ብር ከፍሎ ድጋሚ እንዲያስተካክል እድል ይሰጠዋል፡፡ 50000 ብር ከፍሎ ድጋሚ እንዲያስተካክል የተሰጠዉን እድል መጠቀም ካልቻለ የስራ ፍቃዱ እንዲታገድ ፈቃዱን ለሰጠው አካል የማሳወቅ ስራ ይሰራል፡፡ | |
| 1 | የድርጅቱ ሰራተኞች የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ስልጠና ያላሰለጠነ፤<br>በቂና ተገቢ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎችን ያላሟላ፤<br>የተቋም ደህንነት መኮንን ያልቀጠረ፤<br>በተቋሙ ዉስጥ ያሉት ሰራተኞች በእሳትና አደጋ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ ስልጠና እንዲወስዱ ያላደረገ፣ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ስራቸውን በአግባቡ እንዳይሰሩ ያደረገ፣ ያልተባበረ፣ እሳትን ሊቋቋሙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ግንባታ ያልገነባ፤<br><br>በቂ መተላለፊያዎችና የአደጋ ጊዜ መዉጫዎችን ከነሆሱ ያላዘጋጀ፤<br><br>በድርጅቱ ዉስጥ ከ115-150 ሜ.ኪዩብ የዉሀክምችትና በደቂቃ ከ2000-2500 ሊትር ዉሀ መርጨት የሚችል በነዳጅና ኤክትሪክ የሚሰራ ፋዩር ፓምፕ ያላሟላ፤<br><br>አዉቶማቲክ የዉሀ መርጫ ሲስተም(sprinkiler)ና እንደ ተቋሙ አይነት አስፈላጊ ዲክቴክተሮችን ያላሟላ፤<br><br>የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን ያላሟላ፤<br><br>የኤሌክትሪክ ገመዶችን በአግባቡ ያልዘረጋና በኮንዲዩት ያልሸፈነ፤ የንብረት አያያዝና ዕቃዎች አደራደር በአግባቡ ያልተገበረ፤<br><br>የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በሚሰጡት የሙያ ምክርና ድጋፍ መሰረት ሀይድራንት ያልተከለ | ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ፣ በስድስት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲያስተካክል ሙያዊ ምክር ግብረመልስ ይሰጠዋል፡፡<br><br>ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ከሆነ በሶስት ወራት ጊዜ ዉስጥ እንዲያስተካክል የጽሁፍ ማስጠንቀቅያ ይሰጠዋል፡፡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ካላስተካከለ 100000 ብር ከፍሎ ድጋሚ እንዲያስተካክል እድል ይሰጠዋል፡፡ 100000 ብር ከፍሎ ድጋሚ እንዲያስተካክል የተሰጠዉን እድል መጠቀም ካልቻለ የስራ ፍቃዱ እንዲታገድ ፈቃዱን ለሰጠው አካል የማሳወቅ ስራ ይሰራል፡፡ | |